## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ስርዓት አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2011

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ማውጫ ........................................................................................................ i

የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ (Executive summary)......... I

ክፍል አንድ ........................................................................................................ 1

መግቢያ ........................................................................................................ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረት ........................................................................................................ 1

የ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት ........................ 4

የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ........................................................ 5

የፋይናንስ ምንጭ ........................................................................................................ 6

ሠንጠረዥ1. የ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሦስት አመት የተፈቀደ በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ማነጻጸሪያ፡፡ ........................................................ 6

የኦዲቱ ዓላማ ........................................................................................................ 6

ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Audit Area)........................................................ 7

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ................................................ 7

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........................................................................................................ 8

የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የስራ ሂደት መግለጫ (Process Description) ........................................................................................................ 9

ክፍል ሁለት ........................................................................................................ 10

የኦዲት ግኝቶች ........................................................................................................ 10

2.1 የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እስትራቴጂክ ዕቅድንና የግዥ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የግዥ ዕቅድ መርሃ ግብር በማዘጋጀት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም ................... 10

ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር ስራዎችን በተመለከተ የሚሰራቸውን ስራዎች በዓመታዊ እቅድ በማካተት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣......................... 10

ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ግዥዎችን ከመፈፀሙ በፊት በእቃዎች ዓይነት፣ ብዛት እና ጥራት የግዥ ፍላጎቶችን የሰበሰበ እና የገበያ ጥናት ያደረገ ስለመሆኑ ...................................... 12

በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚገዙ እቃዎች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የተዘጋጀ እና የትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ግዥ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሚቀጠር አማካሪ ድርጅት የተከናወነ ስለመሆኑ፣ ..... 14

የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የተቋቋመ ስለመሆኑ ..... 16

ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች የሚፈጸሙበትን የግዥ ዘዴዎች በመለየት በግዥ እቅድ ውስጥ ማካተቱን በተመለከተ፣ ..... 16

ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያስፈልጉ የትምህርት ግብዓቶች እና ተዛማጅ እቃዎች በታቀደላቸው ጊዜ መገዛታቸውን በተመለከተ፣ ..... 17

አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑ መረጋገጡን በተመለከተ፣ ..... 22

የተገዙ ዕቃዎች በወቅቱ ተሰራጭተው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የተደረገ ስለመሆኑ፣ ..... 26

ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግዥ የተመደበለትን በጀት በወቅቱና በአግባቡ ስራ ላይ ያዋለ ስለመሆኑ፣ ..... 28

የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የአቅም ግንባታ ሥራን በተመለከተ ..... 29

የፕሮጀክቱ ንብረት በሚገባ የተመዘገበ እና ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግለት ስለመሆኑ፣ ..... 30

የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ እና ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ክትትል የተደረገ ስለመሆኑ፣ ..... 34

የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ የሚካሄድበት ስለመሆኑ እና የንብረት አስተዳደር ሰራተኞች መ/ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት የሚደረግ ስለመሆኑ፣ ..... 35

የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ የሚወገድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ፣ ..... 36

ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፣ ..... 37

ክፍል ሦስት ..... 39

መደምደሚያ (Conclusion) ..... 39

ክፍል አራት ..... 41

የማሻሻያ ሃሳቦች (Recommendations) ..... 41

አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ..... 44

አባሪ 2፡ የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ድርጅታዊ መዋቅር ..... 48

# የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ

## (Executive summary)

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት ለሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ይህን የክዋኔ ኦዲት አካሂዷል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ዝርዝር ኦዲቱ በዋናነት የሸፈነው ከ2008-2010 ዓ.ም ያሉትን ሶስት የበጀት ዓመታት የሥራ ክንውኖች ነው፡፡

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- በ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ስራ ለመጀመር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ግዥዎች የሦስት ዓመታት እቅድ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሲሚንቶ እና የአርማታ ብረት ግዥዎችን ከመፈፀሙ በፊት የግብዓቶቹን ዓይነትና ብዛት በዓመታዊ እቅዱ ለይቶ አለማስቀመጡ እና ለፈፀማቸው ግዥዎች የገበያ ጥናት ያላደረገ መሆኑ፣
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተፈጥሮ ሳይንስ መጽሐፍት ግዥ እና የፈርኒቸርና የምግብ ቤት እቃዎች ግዥዎችን የማማከር ስራ ፈቃድ ሳይኖራቸው ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ የተሰጠ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከፍተኛ ግዥዎችን መርምሮ የሚያጸድቅ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ያላቋቋመ መሆኑ፣
- ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያስፈልጉ የፈርኒቸር፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ ኮምፒውተር እና ተዛማጅ እቃዎች በታቀደላቸው ጊዜ ተገዝተው ያልቀረቡ መሆኑ፣

- ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የተገዙ ጀነሬተሮችና የምግብ ቤት እቃዎች በወቅቱ አገልግሎት ላይ አለመዋላቸው፣
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታ ግብዓቶች ወጥነት ባለው መልኩ የሚመዘገቡበት አሰራር አለመኖሩ እና ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ያልተደረገላቸው መሆኑ፣
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት ቆጠራ ተካሂዶበት የሚያውቅ አለመሆኑ፣
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አገልግሎት የማይሰጥ ንብረት የሚወገድበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ

ታውቋል፡፡

በመሆኑም፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሆነ በሌሎች ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች እቅድ ሲያቅድ የሚያዘጋጃቸውን መመሪያዎች እና ሰነዶች ለይቶ ሊያስቀምጥ፣ የግዥ ዕቅድ ሲታቀድ ግብዓቱን ከሚጠቀሙ አካላት የግዥ ፍላጎት ሊያሰባስብ፣ እንዲሁም የገበያ ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡ የሚገዛቸውን ዕቃዎች በአይነትና ብዛት በመለየት አስቀድሞ ሊያስቀምጥ፣ ግዥዎቹ የሚከናወኑበትን ዘዴ እንዲሁም ተግባራት የሚከናወኑበትን ጊዜ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በዕቅዱ መሰረት ስለመከናወኑ ከዕቅዱ ጋር በማነጻጸር በየጊዜው የእቅድ ክንውን ሪፖርት የሚቀርብበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለትምህርት መሳሪያዎች፣ ለፈርኒቸር እና ለምግብ ቤት እቃዎች ግዥ የቴክኒክ መግለጫ ዝግጅት ለማድረግ እና በተዘጋጁት መግለጫዎች መሰረት ዕቃዎቹ ስለመቅረባቸው የሚያረጋግጥ አማካሪ ቅጥር በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የእቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም ማንዋል መሰረት በግልጽ ጨረታ ሊያከናውን እና ፈቃድ ላለው አካል ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች ከፍተኛ ግዥዎችን መርምሮ የሚያፀድቅ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊያቋቁምና ግዥዎች የመንግስት ህግና ስርዓት ጠብቀው መገዛታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላት በማስተባበር ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስፈልጉ የመጽሐፍት፣ የፈርኒቸር፣ የላቦራቶሪ

መሳሪያዎችና ግብዓቶች ግዥ በወቅቱ በመፈፀም ለዩኒቨርሲቲዎቹ ሊያሰራጭ እና አገልግሎት ላይ መዋላቸውን በመከታተል በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠውን ግብ ሊያሳካ ይገባል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተገዙ የምግብ ማዘጋጃ፣ ማብሰያ እና ማቀረቢያ እቃዎችና ጄነሬተሮችን ለተጠቃሚ ዩኒቨርሲቲዎች በወቅቱ ሊያስረክብ እና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታ ግብዓቶች ግዥ፣ ስርጭት እና አጠቃቀም ወጥነት ባለው መልኩ ሊመዘገብ፣ የግዥ እና የጨረታ ሰነዶች በተገቢው መልኩ ሊጠበቁና ሊያዙ፣ እንዲሁም በየግንባታ ሳይቱ የሚገኙ የሲሚንቶ እና የአርማታ ብረቶች ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የንብረት ቆጠራ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች የሚወገዱበት የንብረት አወጋገድ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ቢደረግ ንብረቶቹን ከስርቆትና ከብክነት ለመከላከል እንዲሁም ከተቋራጮች የሚቀርቡ ተደጋጋሚ ጥያዎችን ምላሽ ለመስጠት ያግዛል፡፡

የሚሉ የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. አገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ እንድትሰለፍ ለማድረግ መንግስት የተለያዩ የልማት ፖሊሲዎችንና እስትራቴጅዎችን ነድፎ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በየጊዜው የሚወጡ የልማት ፖሊሲዎችና እቅዶች በአግባቡ ስራ ላይ ሊውሉ የሚችሉትና የተቀመጡ አገራዊ ግቦች ሊሳኩ የሚችሉት በከፍተኛ ደረጃ የተማረ የሰው ኃይል በጥራትና በብዛት ማፍራት ሲቻል መሆኑን በመገንዘብ መንግስት የከፍተኛ ትምህርትን በሀገሪቱ በስፋት በማስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት በሀገሪቱ ሁለት ብቻ የነበረው የዩኒቨርስቲዎች ቁጥር በአሁኑ ወቅት 45 ሊደርስ ችሏል፡፡
2. መንግስት ለከፍተኛ ትምህርት ፍትሃዊ ስርጭት መስፋፋት በሰጠው የተለየ ትኩረት በአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን አስር ተጨማሪ ዩኒቨርስቲዎችን በመገንባትና ነባር ዩኒቨርስቲዎችን የማስፋፋት ስራዎች በማከናወን ዘርፉ የበለጠ እንዲስፋፋ በማድረግ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰለጠኑ ዜጎች ቁጥር ከፍ ለማድረግ ሲሰራ ነበር፡፡
3. በሁለተኛው የዕድገትና ትርንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመንም ተጨማሪ 11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎችን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በመገንባት የከፍተኛ ትምህርት ፍትሀዊነትና ተሳትፎን ለማሳደግ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የእነዚህን ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ እንዲሁም የተለያዩ የትምህርት ግብዓቶች ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ስርዓትን እንዲያስፈጽም ከዚህ ቀደም የአስሩን ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ሲያስፈጽም የነበረው የ10 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በይበልጥ በሰው ኃይል ተጠናክሮ የ11 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሚል ተዋቅሮ እየሰራ ይገኛል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረት

4. ዘመናዊ ትምህርት ማዕከላዊ መንግስታትን ለማጠናከርና አዲስ ስልጣኔን ከውጭ ለማስገባት የሚጠቅም መሆኑ ስለታመነበት ከስድስት ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው ወንዶችና ሴቶች ትምህርት ቤት የመግባት ግዴታ እንዳለባቸው ወላጆች ልጆቻቸው እንዲማሩ ማበረታታት እንደሚገባቸው የሚያመለክት የመጀመሪያው የትምህርት

አዋጅ በ1898 ዓ.ም ወጣ፡፡ አፄ ምኒልክን የተኩት ንግስት ዘውዲቱ የትምህርት ዓላማ ክፉና በጎ የሚለይበት ንጉስና ፈጣሪ የሚፈራበትን ዕውቀት ያስገኛል በሚል በ1921 ዓ.ም ሁለተኛው የትምህርት አዋጅ እንዲወጣ አድርገዋል፡፡

5. አፄ ኃይለስላሴ የአገሪቱ ንጉስ ሲሆኑ ዘመናዊ መንግስት ለመመስረት በነበራቸው ዓላማ በዚያው በነገሱበት ዓመት በ1923 ዓ.ም ቀደም ሲል የትምህርቱን ሥራ እንዲመራ ያቋቋሙት የትምህርት ዋና ዳይሬክቶሬት (Directorate General of Public Education) ወደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በማሳደግ የትምህርትና ስነ ጥበብ ሚኒስቴርን አቋቋሙ፡፡

6. የትምህርቱ ሥራ እየሰፋ ሲሄድ አወቃቀሩንና የፋይናንስ አቋሙን ለማጠናከር ሲባል በ1935 የትምህርት ሚኒስቴርን ሥልጣንና ተግባር የሚወስን አዋጅ እንዲሁም በዚሁ ዓመት የትምህርትና ስነ ጥበብን ጉዳይ የሚከታተልና የሚመራ የትምህርትና ሥነ ጥበብ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ወጣ፡፡

7. ለ1966 አብዮት መከሰት ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ በትምህርቱ ዘርፍ የነበረው ችግር በመሆኑ በ1967 ዓ.ም ደርግ ወደ ሥልጣን ሲመጣ የትምህርቱን ስርዓት ለመለወጥ አዲስ አደረጃጀት ተጠንቶ ስራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡ ሥነ ጥበብ ወደ ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር ሲሄድ የከፍተኛ ትምህርት ሥራ ዘርፎች ራሳቸውን ችለው በኮሚሽን ደረጃ እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ትምህርት ሚኒስቴር በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በአስር መምሪያዎች በረዳት ሚንስትሮችና በሚኒስቴር ዴኤታና በሚኒስትር ይመራ የነበረው የትምህርት ሥራ ወደ አራት መምሪያዎችና ወደ አምስት ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡

8. በ1983 ኢህአዴግ አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ተንሰራፍተው የቆዩ ችግሮችን ለመፍታት የትምህርት ፖሊሲውን መቀየር አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት በአዋጅ 41/85 የከፍተኛ ትምህርትን ጨምሮ አስራ ሰባት ተግባራት እንዲኖሩት በማድረግ ተቋቁሟል፡፡ በአዋጅ 4/87 እና 256/94 እነዚህ ተግባራት ወደ አስራ አምስት ተግባራት ተቀንሰው ትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለአቅም ግንባታ ሚኒስቴር እንዲሆን ተደረገ፡፡

9. በኋላም የሀገራችን ትምህርት ለሀገር ሁለንተናዊ ልማት የሚበጁ ዜጎችን እንዲያፈራ ለማስቻል የተለያዩ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲዎች ሲቀረፁ ቆይተው በኢትዮጵያ ህዝቦች የእድገት ፍላጎትና ዓለም አቀፋዊ ትስስር መሰረት ተቋማት

አስተማማኝ የማስፈፀም አቅም እንዲኖራቸው ለማስቻል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ተግባር እንደገና መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መስከረም 25, 2008 ዓ.ም በአዋጅ 691/2003 እንዲሁም በአዋጅ 916/2008 ዓ.ም ትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሆኖ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

10. ሆኖም በጥቅምት 2011 ዓ.ም የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍና የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ከትምህርት ሚኒስቴር በመውጣትና ቀድሞ የሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ሚኒስቴር ስር ከነበረው የሳይንስ ዘርፍ ጋር አንድ ላይ በመሆን የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በመባል ተቋቁመዋል፡፡

## የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር

11. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት አሉት፡፡

- የከፍተኛ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል፤
- የከፍተኛ ትምህርት ከአገሪቱ አጠቃላይ የልማት ፖሊሲ እና ከዘርፎች እድገት ጋር አብሮ ለማስኬድ የሚያስችል እስትራቴጂ ይነድፋል፣ በስራ ላይ ያውላል፡፡
- የአገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጂን ይቀርፃል፤ በሚመለከታቸው አካላት ሲፀድቅም በስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡
- የከፍተኛ ትምህርትና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በመሰረታዊ የሳይንስ ጥናትና ምርምር የጎለበቱ እንዲሆኑ የሚያስችል ስልት ይነድፋል፣ ይተገብራል፤ የሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ውጤቶች በስራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ ያመቻቻል፤
- የከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የእርስበርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሰራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤

- የከፍተኛ ትምህርትና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ደረጃ ያወጣል፤ በተቋማቱ ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መሰጠቱን ይከታተላል፤
- የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አፈፃፀም ይከታተላል፤
- የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላ እና ምደባ አፈጻጸም ፍትሃዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

## የ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

12. በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ለሚገነቡ ዩኒቨርሲቲዎች ማስፈፀሚያ እቅድ በተጠቀሰው መሰረት የ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለቀድሞው የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሆኖ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ያከናውናል፡፡

- የአዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ የሚፈፀምበትን ዝርዝር የፕሮጀክት ሰነድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤
- የፕሮጀክት ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤
- የአማካሪዎችንና የተቋራጮችን ምርጫ ያስፈፅማል፤
- በአማካሪዎች የተዘጋጁ ዲዛይኖች (ስታንዳርድና ዝርዝር ዲዛይኖች) በውይይት ዳብረው እንዲፀድቁ ያደርጋል፤
- የግንባታ ሥራ ተቋራጮችን ምርጫ ከከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር ይፈፅማል፤
- ለሥራ ተቋራጮች በዲዛይኑና በግንባታው አፈፃፀም ላይ ሥልጠና በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ ያደርጋል፤
- ለሥራ ተቋራጮች፣ ለአማካሪዎችና ዕቃ አቅራቢዎች በውለታና በሕግ አግባብ መሠረት ክፍያ ይፈፅማል፤
- ይዞታቸው ለዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በመሰጠቱ ለሚነሱ ነዋሪዎች በክልሉ የካሳ ክፍያ ታሪፍ መሰረት ክፍያ እንዲፈፀም ያደርጋል፤
- ለዩኒቨርሲቲዎች የሚያገለግል የውሃ፣ የኤሌክትሪክ ሃይልና የቴሌኮም አገልግሎት እንዲሟላ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በጋራ ይሰራል፤

- ለግንባታ የሚያስፈልጉ የአርማታ ብረትና ሲሚንቶ ያቀርባል፣ ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ ግንባታ ሳይት መጓጓዛቸውንና ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡
- የትምህርት መሣሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ዝርዝር ስፔሲፊኬሽንና ስታንዳርድ እንዲዘጋጅ ግዥው እንዲፈፀም ያደርጋል፣ በበቂ መጠንና ጥራት በየዩኒቨርስቲው መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
- የሚገነቡ ሕንፃዎችን ዓይነት፣ ብዛትና፣ የግንባታ ቅደም ተከተል አዘጋጅቶ እንዲገነቡ ያደርጋል፤
- የመሰረተ ልማትና የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ፕላንት ግንባታ ቢቻል ከግንባታው በፊት አለዚያም ጎን ለጎን እንዲካሄድ ያደርጋል፤
- የአማካሪዎች ፎረም በማቋቋም በግንባታው አፈፃፀም የሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
- ዩኒቨርሲቲዎች ፕሮጀክቱን ለመረከብ በሚችሉበት ቁመና ላይ ሲደርሱ ዝርዝር የርክብክብ ሰነድ አዘጋጅቶ ፕሮጀክቱን ያስረክባል፤
- ለአዳዲሶቹ ዩኒቨርሲቲዎች የተፈቀደውን የግንባታና የትምህርት መሳሪዎች ግዥ በጀት የፋይናንስ ደንብን ተከትሎ ሥራ ላይ ያውላል፣ ወቅቱን ጠብቆ ሂሳቡ መዘጋቱን ያረጋግጣል፤ ሪፖርትም ያቀርባል፤
- ለፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ተገቢው የሰው ሃይል እንዲሟላ ያደርጋል፤
- ግንባታውና የግብዓት አቅርቦቱ በአግባቡ መፈጸሙን ለመከታተል የሚያስችል የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ስለአፈጻጸሙም ሪፖርት ያቀርባል፤
- እንደውለታቸው በማይፈፅሙ ሥራ ተቋራጮችና አቅራቢዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

የሚሉ ናቸው፡፡

## የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

13. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በአንድ ዋና ስራ አስኪያጅ እና የተለያዩ የስራ ክፍሎች በሚይዙ ሶስት ምክትል ዋና ስራ አስኪያጆች እንዲመራ የተቋቋመ ሲሆን እነርሱም የምህንድስና ጉዳዮች ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ፣ የግብዓቶች አቅርቦት ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ፣ እና የፋይናንስ እና

የሰው ኃይል አስተዳደር ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

14. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሚያዚያ 2010 ዓ.ም በማዕከል እና በተለያዩ ሳይቶች የግንባታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አሉት፡፡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በአጠቃላይ 173 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን ከነዚህም መካከል 14ቱ ሴቶች ሲሆኑ 159ኙ ወንዶች ናቸው፡፡ የሰራተኞችን ብዛት በትምህርት ደረጃ ስንመለከት የማስተርስ ዲግሪ ያላቸው 8፣ የባችለር ዲግሪ ያላቸው 44፣ ዲፕሎማ ያላቸው 9፣ እንዲሁም የተቀሩት 112 ሰራተኞች ከ8-12ኛ ክፍል የትምህርት ደረጃ አላቸው፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

15. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2008 እስከ 2010 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2008 | 1,762,000,000 | 439,404,400.89 | 24.94% |
| 2009 | 2,440,898,251.30 | 2,029,964,642.20 | 83.16% |
| 2010 | 2,878,896,570.00 | 2,471,468,936.35 | 85.85% |
| 2011 | 2,917,981,900.00 | | |

<u>ሠንጠረዥ1.</u> የ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የሦስት አመት የተፈቀደ በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ማነጻጸሪያ፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

16. የኦዲቱ ዓላማ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን በመንግስት እየተገነቡ ያሉ አስራ አንድ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ዙሪያ የሚከሰቱ የአሠራር ክፍተቶችን ለይቶ በማውጣት ክፍተቶቹ የሚቀረፉበት የማሻሻያ ሀሳቦችን (Recommendations) ለማቅረብ ነው፡፡

### ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Audit Area)

17. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች

### የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

18. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና ሁለት የኦዲት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች (sub issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም:-

1. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት እስትራቴጂክ ዕቅድንና የግዥ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የግዥ ዕቅድ መርሃ ግብር በማዘጋጀት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፣
   - 1.1 የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ለሚፈጽማቸው ግዥዎች የግዥ ፍላጎት እና የግዥ መርሀ ግብርን መሰረት በማድረግ የግዥ እቅድ የሚያዘጋጅና በዕቅዱ መሰረት መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር የተዘረጋ መሆኑን መገምገም፣
   - 1.2 የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የግዥ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣
2. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የንብረት አስተዳደር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
3. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የግዥና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

የሚሉ ናቸው፡፡

### የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

19. የተመረጡትን ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 35 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቋቋመበት አዋጅ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁ. 649/2001፣ የ11አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከ2008-2012 እስትራቴጅክ ዕቅድ፣ የ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስልጣንና ተግባር፣ የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁ.9/2003፣ የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከእቃ አቅራቢዎች ጋር የተዋዋላቸው የግዥ ውሎች፣ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ዓመታዊ እቅድ እና መልካም የሥራ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልከው አስተያየት እንዲሰጥባቸው የተደረገ ሲሆን ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

### የኦዲቱ ወሰን

20. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በትምህርት ሚኒስቴር በተቋቋመው የ11 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሲሆን ኦዲቱ በዋናነት የሸፈነው ከ2008 እስከ 2010 በጀት ዓመታት ያለውን የስራ አፈጻጸም እና በ2011 በጀት ዓመት እስከ ጥቅምት 30/2011 ድረስ የተሰሩ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ስራዎችን ነው፡፡

### የኦዲቱ ዘዴ

21. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በ11 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሲሆን የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ስርዓትን የሚመለከቱ የተለያዩ አዋጆች፣ መመሪያዎች፣ ከ2008-2012 የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የእስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ከ2008-2010 በጀት ዓመታት የተሰሩ ዓመታዊ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱን በሚመለከት የወጡ የተለያዩ ብሮሸሮች መጽሄቶችና የተለያዩ ሰነዶች በመከለስ፣ ከ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች በናሙና በተመረጡ 3 ዩኒቨርስቲዎች (ሠላሌ ዩኒቨርስቲ፣ እንጅባራ ዩኒቨርስቲ እና ወራቤ ዩኒቨርስቲ) እና በነዚህ ዩኒቨርስቲዎች በሚገኙ የግንባታ ቅርንጫፍ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ቃለ-

መጠይቅ በማቅረብ እና በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ ማስረጃዎችን በመሰብሰብ ነው፡፡

## የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የስራ ሂደት መግለጫ (Process Description)

22. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ግንባታዎችን የማከናወን እና ዩኒቨርስቲዎቹን ስራ ለማስጀመር የሚያስችሉ የትምህርት ግብዓቶችን የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡ በዚህም መሰረት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ11ዱም አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ቅርንጫፍ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶችን በማቋቋም የቦታ መረጣ፣ ቦታ ርክክብ እና ካሳ ክፍያ ከፈፀመ በኋላ በተመረጠው የህንፃ ዲዛይን መሰረት የህንፃ ስራ ተቋራጮችን በማሰማራት ግንባታዎችን ያከናውናል፤ ለግንባታ ግብዓትም የሚሆን የአርማታ ብረት እና ሲሚንቶ ግዥ በመፈፀም ወደግንባታ ሳይቶች ያሰራጫል፤ ለንብረቶቹ ጥበቃና ቁጥጥር ያደርጋል፤ የግንባታውን ሂደት የሚከታተሉ አማካሪ ድርጅቶችን በየግንባታ ሳይቶች በማሰማራት ክትትል ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ለዩኒቨርስቲዎቹ የሚያስፈልጉትን የኤሌክትሪክና የውሀ አቅርቦቶች ደረጃ በደረጃ ያሟላል፡፡

23. ከዚህ በተጨማሪም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ዩኒቨርስቲዎቹን ስራ ለማስጀመር የሚያስችሉ የመጽሐፍት፣ የፈርኒቸር፣ የላቦራቶሪ እቃዎች፣ የምግብ ቤት እቃዎች፣ ጀኔሬተር፣ ኮምፒውተር እና ተዛማጅ እቃዎችን ግዥ ይፈጽማል፡፡ በግዥ ሂደቱም የሚገዙ ግብዓቶችን የመለየት እና ዝርዝር ስፔስፊኬሽን የማዘጋጀት፣ የቴክኒካል ግምገማ የማካሄድ፣ የዋጋ ትንተና የማካሄድ እና ግዥው ውሳኔ ሲያገኝ የመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ከእቃ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር የተፈራረመውን ውል የማስተዳደር፣ ለውጪ አገር ግዥዎች የተሟሉ ሰነዶች ይዞ ኤልሲ የመክፈት፣ የተገዙ እቃዎች ለዩኒቨርሲቲዎች መላካቸውን ከሚላከው የግዥ ዶክመንት አጣርቶ በውሉ መሰረት ክፍያው መፈፀሙን የማጣራት፣ የጉምሩክ ክፍያዎችን የማጠናቀቅና የትራንዚት ስራ መሰራቱን የማጣራት፣ ለዩኒቨርስቲዎች መሰራጨቱን የመከታተል፣ የተከላ፣ ፍተሻና የአጠቃቀም ስልጠና መሰጠቱን የመከታተል፣ እንዲሁም በስፔስፊኬሽኑ መሰረት እቃዎች መቅረባቸውን በማረጋገጥ ክፍያ የመፈፀም ስራዎችን ይሰራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### 2.1 የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እስትራቴጂክ ዕቅድንና የግዥ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የግዥ ዕቅድ መርሃ ግብር በማዘጋጀት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም፣

**ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር ስራዎችን በተመለከተ የሚሰራቸውን ስራዎች በዓመታዊ እቅድ በማካተት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣**

24. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር ስራዎችን በተመለከተ የሚሰራቸውን ስራዎች የእስትራቴጅክ እቅዱን ወደ ዓመታዊ እቅድ በመመንዘር ሊያቅድ እና በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ያከናወነውንም ስራ በተመለከተ የአፈጻጸም ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

25. ይሁን እንጂ

- በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ተዛማጅ እቃዎች፣ የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ ፈርኒቸር፣ ለተፈጥሮ ሳይንስ የስልጠና መስኮች የሚያስፈልግ የማጣቀሻ መጽሐፍት፣ ዩኒቨርስቲዎች ስራ ለመጀመር የሚያስፈልጓቸውን ኮምፒውተሮችና ተዛማጅ እቃዎች፣ የምግብ ቤት እቃዎች፣ እንዲሁም የጀነሬተር ግዥ ለመፈፀም ታቅዶ ምንም ዓይነት ግዥ አለመከናወኑ፣
- ግዥ ባልተከናወነበት በእቅድ ክንውን ሪፖርቱ ከ67 ፐርሰንት እስከ 85 ፐርሰንት አፈፃፀሙ እንደተከናወነ ተደርጎ የቀረበ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2008 በጀት ዓመት የመግባቢያ ሰነዶችን እና መመሪያዎችን ለማዘጋጀት እቅድ ቢይዝም ከየትኞቹ ባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ እና ምንን በተመለከተ እንደሚፈራረሙ በዕቅዱ አለመገለጹ፣ ምንን በተመለከተ እና ምን ያህል መመሪያዎች ለማዘጋጀት እንደታቀደ ያላስቀመጠ መሆኑ፤

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት የአርማታ ብረት እና የሲሚንቶ ግዥ ለመፈፀም እቅድ ቢይዝም ስለሚገዛው የሲሚንቶና የአርማታ ብረት ዓይነት እና መጠን በእቅዱ ላይ ያላስቀመጠ መሆኑ፣
- በ2010 በጀት ዓመት እቅድ የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ፈርኒቸሮች እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ እቃዎችን ግዥ ለመፈፀም አቅዶ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ባልተከፈተበት ሁኔታ በእቅድ ክንውን ሪፖርቱ 51 ፐርሰንት እንዳከናወነ ተደርጎ የቀረበ መሆኑ፤
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች ተግባራት የተከናወኑበትን ጊዜ የማያመለክቱ መሆኑ፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

26. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው

- በ2008 እና በ2009 ግዥው እንዲከናወን ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ቢላክም በተራዘመ ሂደት ውል ተይዞ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረሰ በጣም ተጓትቶ እንደሆነ፣
- የባለ-ድርሻ አካላትና አጋሮች ለተለዩ የሚዘጋጅ በመሆኑ የመግባቢያ ሰነዶችና መመሪያዎች አይነት እና ብዛት ያልተቀመጠ መሆኑን፣
- የሚገዛው የአርማታ ብረትና ሲሚንቶ ብቻ በመሆኑ አይነትና ብዛቱ አለመገለጹን፣
- ሌተር ኦፍ ክሬዲት ሳይከፈት 51 ፐርሰንት ተሰጠ ለሚለው በግዥ ሂደት ውስጥ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ለመክፈት የሚካሄደው የግዥ ፍላጎትን ከመለየት ጀምሮ ጨረታ ማዉጣትና አሸናፊን መለየት፣ ዉል መያዝ እና ሌሎች ተግባራትን አካቶ ዝርዝር ውጤት ተደምሮ የተሰጠ መሆኑን፣
- የዕቅድ ክንውን ሣምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ በሩብ ዓመት፣ በመንፈቅ ዓመትና በዓመት ውስጥ የሚቀርብ በመሆኑ የክንውኑንም ጊዜ አመላካች ሆኖ የተሰራ መሆኑን

ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ ለረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ እና በመውጫ ስብሰባ ገልፀዋል፡፡

27. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ግዥዎች የተጓተቱ መሆኑ እየታወቀና ምንም አይነት ግዥ ሳይፈፀም የግዥ አፈፃፀሙ ከ67%-85% እንደተከናወነ ተደርጎ ሪፖርት መደረጉ አግባብ ባለመሆኑ፣ ባለድርሻ አካላት እና አጋሮች ከአመታዊ እቅድ በፊት በእስትራቴጅክ እቅድ ተለይተው መቀመጥ ያለባቸው በመሆኑ እና የስራ

መመሪያዎችን ለማዘጋጀት የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባራት እንጂ የባለድርሻ አካላት አለመታወቅ እንደምክንያት ሊወሰድ የማይችል በመሆኑ፣ የሚገዛው የብረት አይነት እንደሚገነባው ህንፃ ብዛት እና አይነት የተለያየ (ባለ 6፣ ባለ 8፣ ባለ 10፣ ባለ 12 ወዘተ) በመሆኑና አይነትና ብዛቱ አለመገለፁ አመታዊ በጀት በትክክል ለመመደብ የማያስችል በመሆኑ፣ በግዥ ሂደት ለተሰሩ ስራዎች የተሰጡ የክንውን ምጣኔዎች (percentage) አሳማኝ ያልሆኑ እና ትክክለኛ ማስረጃም ያልቀረበባቸው በመሆኑ፣ እንዲሁም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች ተግባራት የተከናወኑበትን ጊዜ በሩብ ዓመታትም ቢሆን ከፋፍለው የሚያሳዩ ባለመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አያስችልም፡፡

28. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በዓመታዊ እቅድ የያዛቸውን ተግባራት በወቅቱ ካላከናወነ ሀብት አላግባብ እንዲባክን ሊያደርግ፣ 11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎት በወቅቱ እንዳያገኙ ሊያደርግ ይችላል፤ እንዲሁም ትክክለኛ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ካላቀረበ ሪፖርቱን የሚጠቀሙ አካላት የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዙ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ግዥዎችን ከመፈፀሙ በፊት በእቃዎች ዓይነት፣ ብዛት እና ጥራት የግዥ ፍላጎቶችን የሰበሰበ እና የገበያ ጥናት ያደረገ ስለመሆኑ፣**

29. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችሉ ግዥዎችን ለመፈፀም በእቃዎች ዓይነት፣ ብዛት እና ጥራት የግዥ ፍላጎቶችን ሊሰበስብና የገበያ ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡

30. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ

- በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት የአርማታ ብረት እና የሲሚንቶ ግዥ ለማከናወን እቅድ ቢይዝም ስለሚገዛው የሲሚንቶ እና የብረት አይነት (ባለ 6፣ ባለ 8፣ ባለ 10 ወዘተ) እና ብዛት በዝርዝር ያላስቀመጠ መሆኑ፣
- በ2008 በጀት ዓመት ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያገለግል 12,440 ቶን የባለ 10 ጨምሮ የተለያየ ስፋት ያላቸው (ከእያንዳንዱ ምን ያህል ብዛት ብረት እንደተገዛ መረጃ ያልቀረበ) የአርማታ ብረት ግዥ የፈፀመ መሆኑ፣ ሆኖም በ2008 ከተገዛው ብረት እስከ ጥቅምት 2011 ድረስ ከግንባታ ተርፎ አገልግሎት ላይ ሳይውል የተከማቸ የባለ 10 የአርማታ ብረት በየግንባታ ሳይቱ ቢኖርም በ2011 ዓ.ም በድጋሚ ለግንባታ ከሚያስፈልገው ውጪ በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ የግንባታ ቅርንጫፍ ፕሮጀክቶችን የግዥ ፍላጎት ሳይጠይቅ ተጨማሪ ብዛቱና

የገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ባለ 10 የአርማታ ብረት ግዥ ፈጽሞ ለዩኒቨርስቲዎች ያሰራጨ መሆኑ፤

- በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት ዩኒቨርስቲዎች መካከል በመስክ ጉብኝት ወቅት ለሰላሌ ዩኒቨርስቲ የግንባታ ፕሮጀክት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የተከማቸ 12,263 ቤርጋ (1ቤርጋ =12 ሜትር የአርማታ ብረት) ባለ 10 ብረት እያለ እና አገልግሎት ላይ ሳይውል በ2011 ተጨማሪ 2,900 ቤርጋ ባለ10 የአርማታ ብረት ከቅርንጫፍ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፍላጎት ውጭ በግንባታ ሳይት የተራገፈ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለፈፀማቸው ግዥዎች የገበያ ጥናት ያላደረገ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በመስክ ጉብኝት በተደረገ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

31. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በየሳይቱ ስለሚገኝ የባለ 10 የአርማታ ብረት ተጠይቀው ይህ ብረት የሁለተኛ ዙር ግንባታን ባካተተ መልኩ ግዥው ተፈጽሟል ሆኖም ሁለተኛ ዙር ግንባታ በበጀት እጥረት ምክንያት ሊገነባ ባለመቻሉ የተገዛው ብረት አገልግሎት ላይ ሊውል ባይችልም በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ላይ እንደዋለ፣ በሌላ በኩል በዚህ ብረት መጠቀም የሚቻልባቸው ሁኔታዎች በሌላ መተካት ምክንያት ትርፍ ሆኖ ቢገኝም በቀጣይ ግንባታዎች አገልግሎት ላይ እንዲውል እስከዚያው በተገቢው ሁኔታ እንዲያዝ እየተሰራበት መሆኑን፣ እንዲሁም በቂ የገበያ ጥናት በማድረግና ወቅታዊ ሁኔታዎችን በማጤን ግዥ የሚፈጸም መሆኑን በኦዲት ወቅት በቀረበ ቃለ-መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡
32. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የሁለተኛ ዙር ግንባታ ባልተጀመረበትና ብዛት ያለው የባለ10 ብረት በየግንባታ ሳይቱ በተከማቸበት ሁኔታ ተጨማሪ የባለ10 ብረት ገዝቶ ማሰራጨት አግባብ ባለመሆኑ እንዲሁም የገበያ ጥናት ሪፖርት እንዲቀርብ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አይቻልም፡፡
33. የስራ ቅደም-ተከተልንና ፍላጎትን መሰረት ያላደረጉ ግዥዎች ለሌላ ሥራ መዋል ይችል የነበረ የመንግሰት ሀብት እንዲያዝ፣ ንብረት እንዲባክን፣ እንዲበላሽ፣ ለጥበቃ ተጨማሪ ወጭ እንዲወጣ ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም ለሚከናወኑ ግዥዎች የገበያ ጥናት አለመጠናቱ ለሚገዙ እቃዎች ትክክለኛ በጀት እንዳይያዝ፣ የተሻለ ጥራትና ዋጋ እንዳይገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚገዙ እቃዎች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የተዘጋጀ እና የትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ግዥ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሚቀጠር አማካሪ ድርጅት የተከናወነ ስለመሆኑ፣**

34. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የፀደቀ የግዥ እቅድ መሰረት በማድረግ የሚገዙ እቃዎች ወይም አገልግሎቶችን የያዘ ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ሊያዘጋጅ ወይም እንዲዘጋጅ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ግዥ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም ማንዋል መሰረት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኃላፊነት በጨረታ በሚቀጠር አማካሪ ድርጅት ሊከናወን ይገባል፡፡

35. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ

- የፀደቀ የግዥ እቅድ መሰረት በማድረግ የሚገዙ እቃዎች ወይም አገልግሎቶችን የያዘ ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ እንዲዘጋጅ ቢያደርግም እቃዎቹ ለሚገዙላቸው 11ዱ ዩኒቨርሲቲዎች እቃዎቹን ከመረከባቸው በፊት ለኮምፒውተር እና ፈርኒቸር እቃዎች የቴክኒክ መግለጫ ከመላኩ ውጪ ለሌሎች እቃዎች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫውንም ሆነ የግዥ ውሉን አስቀድሞ አለመላኩ፣
- የትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ግዥ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኃላፊነት ለዚሁ ስራ በጨረታ በሚቀጠር አማካሪ ድርጅት (ለእስፔስፊኬሽን ዝግጅት፣ ለቴክኒካል ሰነድ ግምገማ፣ እና እቃዎቹ ሲቀርቡ በስፔስፊኬሽኑ እና በውል ሰነዱ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም እቃዎች በተገቢው ሁኔታ ተተክለው ተፈትሸውና አስፈላጊው ስልጠና ለተጠቃሚዎች መሰጠቱን ለማረጋገጥ) እንደሚፈፀም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም ማንዋል የተገለፀ ቢሆንም
    - ለተፈጥሮ ሳይንስ መጽሐፍት ግዥ እንዲሁም ለፈርኒቸርና የምግብ ቤት እቃዎች ግዥ የቴክኒክ መግለጫና የእስታንዳርድ ዝግጅት፣ እቃ አቅራቢዎች የሚያቀርቡትን የቴክኒክ ሰነድ ለመገምገም፣ እንዲሁም እቃዎች ለ11ዱ ዩኒቨርሲቲዎች ሲቀርቡ በቴክኒክ መግለጫው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ የአማካሪነቱን ስራ ሌሎች ተቋማትን ሳያሳትፍና ፈቃድ ሳይኖራቸው ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ የተሰጠ መሆኑ፣
    - ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ እና ኮምፒውቴሽናል ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት መስኮች (ስነ-ሕይወት፣

ፊዚክስ እና ኬሚስትሪ) ለሚገዙ የትምህርት መሳሪያዎች የብር 2,621,774.00፣ እንዲሁም ከአርሲ ዩኒቨርሲቲ ጋር ለምግብ ቤት እቃዎችና ለተለያዩ ፈርኒቸሮች እስፔስፊኬሽን ዝግጅት፣ የቴክኒካል ሰነድ ግምገማ፣ እና እቃዎቹ ሲቀርቡ በስፔስፊኬሽኑ እና በውል ሰነዱ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም እቃዎች በተገቢው ሁኔታ ተተክለው ተፈትሸውና አስፈላጊው ስልጠና ለተጠቃሚዎች መሰጠቱን ለማረጋገጥ የብር 2,800,000.00 የአማካሪነት ውል የተፈራረመ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲዎቹ በውል ስምምነቱ መሰረት እቃዎቹ ገቢ ሲደረጉ በእስፔስፊኬሽን መሰረት መሆናቸውን በዩኒቨርሲቲዎቹ ተገኝተው ያላረጋገጡ መሆኑን

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው

- የግዥ ውሉ የሚተዳደረው በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በመሆኑ የሚገዙ ዕቃዎችን ከየሳይቱ ለመጡ ባለሙያዎች ከዕቃዎቹ ጋር በማስተዋወቅ ርክክብ ሲፈፀም መከተል ስለሚገባቸው ሂደት በቂ ግንዛቤ ወስደው የሚገዙ ዕቃዎችን ዝርዝር ስፔስፊኬሽን በመውሰድ ወደየሳይታቸው ተመልሰዉ እንዲሰሩበት መደረጉን፣
- የቴክኒክ ግምገማውን ለማድረግ የአዲስ አበባና የአርሲ ዩኒቨርሲቲዎች ያለውደድር የቴክኒክ ስራውን እንዲሰሩ የተደረገው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባለሙያዎች በዘርፉ የረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸው በመሆኑ፣ የፈርኒቸርና የምግብ ቤት ዕቃዎችን በተመለከተ የአዳማ ዩኒቨርሲቲ የቴክኒክ ትምህርት ክፍል በዚህ ሙያ በቂ ልምድ ያላቸው በመሆናቸውና ይህ የቴክኒክ ትምህርት ክፍል የአርሲው ካምፓሰ ወደ ሙሉ ዩኒቨርሲቲነት ሲያድግ እነዚህ ሙያተኞች ወደ አርሲ ዩኒቨርሲቲ እንዲመደቡ በመደረጉ ከዩኒቨርሲቲዎቹ ጋር ውለታ በመያዝ ወደ ስራ መገባቱን

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

37. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ከፈርኒቸር እቃዎች ውጭ በአዲሶቹ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚገኙ ባለሙያዎች የሚገዙ እቃዎችን ናሙና ያላሳዩና ከኮምፒውተርና ፈርኒቸር ውጭ ሌሎች እቃዎች ከመላካቸው በፊት የቴክኒክ መግለጫዎች ያልተላኩ በመሆኑ፣ እንዲሁም የአማካሪ ግዥ ከሌሎች የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች እነዚህ የተመረጡበት መስፈርት እና ለማማከር የተሰጣቸው ፈቃድ

ባለመቅረቡ፣ እንዲሁም አማካሪ ዩኒቨርሲቲዎቹ እቃዎች ገቢ ሲደረጉ የማረጋገጡን ስራ በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

38. የግዥ እቃዎች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ አስቀድሞ እቃዎችን ለሚረከቡ አካላት አለመላኩ ስለግዥው ምንነት እና ትክክለኛነት ማወቅ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ፈቃድ ከሌላቸው አካላት የሚፈፀሙ ግዥዎች ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

### የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የተቋቋመ ስለመሆኑ

39. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚያከናውናቸውን ግዥዎች መርምሮ የሚያፀድቅ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይገባል፡፡

40. የፌደራል መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁ. 649/2001 የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸውን ግዥዎች መርምሮ የሚያፀድቅ ኮሚቴ ያቋቁማሉ በማለት ቢገልጽም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አላቋቋመም፡፡

41. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ሲመልሱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተቀመጠ አቅጣጫ መሰረት የግዥ ውሳኔ አቅራቢ ኮሚቴ የተቋቋመ ቢሆንም ከፍተኛ ግዥዎችን መርምሮ የሚያፀድቅ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አለመቋቋሙን ገልጸዋል፡፡

42. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አለመቋቋሙ የመንግስት ግዥ ፍትሃዊና ግልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ተቋሙ ከግዢው ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ማግኘቱን እና ግዥው ህግና ስርዓትን ተከትሎ መፈጸሙን ማረጋገጥ እንዳይቻል ሊያደርግና ለብልሹ አሰራርና ለሙስና በር ሊከፍት ይችላል፡፡

### ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች የሚፈጸሙበትን የግዥ ዘዴዎች በመለየት በግዥ እቅድ ውስጥ ማካተቱን በተመለከተ፣

43. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በግዥ እቅድ ዝግጅት ወቅት ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች ውስጥ አግባብነት ያለውን በመምረጥ በእቅዱ ላይ ሊያመላክት ይገባል፡፡

44. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በግዥ እቅድ ዝግጅት ወቅት ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች (ግልጽ ጨረታ፣ ውስን ጨረታ፣ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ፣ ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ፣ በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ፣ በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ) ውስጥ አግባብነት ያለውን በመምረጥ በእቅዱ ላይ ያላስቀመጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

45. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚገዙ ማንኛውም ዓይነት የትምህርት መሣሪያዎችና የተማሪዎች መገልገያ ዕቃዎች በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በኩል የሚከናወኑ በመሆኑ የግዥ ዘዴዎችን አለማስቀመጣቸውን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሲሚንቶ እና የአርማታ ብረት ግዥ በራሱ የሚፈፅም በመሆኑ እና ለነዚህም ግዥዎች የሚጠቀምባቸውን የግዥ ዘዴዎች በእቅዱ ላይ ያላመላከተ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አያስችልም፡፡

46. በግዥ እቅድ ላይ ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች አግባብነት ያለውን በመምረጥ በእቅድ ላይ ካልተጠቀሰ ግዥዎች ከአዋጅ እና ከመመሪያ ውጭ እንዲፈፀሙ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያስፈልጉ የትምህርት ግብዓቶች እና ተዛማጅ እቃዎች በታቀደላቸው ጊዜ መገዛታቸውን በተመለከተ፣

47. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያስፈልጉ የፈርኒቸር፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ ኮምፒውተር እና ተዛማጅ እቃዎች ግዥ በታቀደላቸው ጊዜ ሊፈፅም ይገባል፡፡

48. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ 11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ስራ ለመጀመር የሚያስቻሏቸውን የትምህርት ግብዓቶች በወቅቱ ያላቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

49. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት የትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ግዥ መፈፀምን በተመለከተ የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና የማጣቀሻ መጽሐፍት ግዥ ለመፈፀም የሚያስችል እስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቶ የጨረታ ሰነድ በመሸጥ ላይ እንደሚገኝ፣ የላቦራቶሪ ፈርኒቸር እስፔስፊኬሽን ዝግጅት የተጠናቀቀ እና ግዥ ለመጀመር የሚያስችል ስራ በመሰራት ላይ እንደሚገኝ፣ የፈርኒቸር፣ የምግብ ማብሰያና ማቅረቢያ እቃዎች እስፔስፊኬሽን በመዘጋጀት ላይ እንደሆነ፣ የኮምፒውተርና ተዛማጅ እቃዎች እስታንዳርድ እና እስፔስፊኬሽን ለማዘጋጀትም ቅድመ ዝግጅት እንደተደረገ በሁለቱ በጀት ዓመታት የእቅድ ክንውን ሪፖርት የተገለፀ ቢሆንም

- እቃዎች እስከ ታህሳስ 2010 ያልቀረቡ መሆኑ፣
- ከታህሳስ 2010 በኋላ እስከ በጀት ዓመቱ ማብቂያ የተሟላ ባይሆንም የተማሪ መገልገያ ፈርኒቸር እና ኮምፒውተር ብቻ የቀረበ መሆኑ፤ እንዲሁም
- የተፈጥሮ ሳይንስ መጽሐፍት ለማቅረብ የውል ስምምነት ካደረጉት ሶስት አቅራቢዎች ሁለቱ በህዳር 2011 ማቅረብ የጀመሩ መሆኑ

ታውቋል፡፡

50. እንዲሁም

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚገዛቸውን እቃዎች ዝርዝር እና የሚያቀርብበትን ጊዜ ለዩኒቨርሲቲዎቹ በግልፅ ባለማሳወቁ እና በወቅቱ ባለማቅረቡ ዩኒቨርሲቲዎቹ በራሳቸው የመደበኛ በጀት (የብር መጠኑን ያልገለጹት) የኤሌክትሮኒክስ፣ የፈርኒቸር፣ የመጽሐፍት፣ የኮምፒውተር፣ ኤልሲዲ ፕሮጀክተር፣ እንዲሁም ለተማሪዎች የምግብ ማብሰያ የሚውሉ እቃዎችን የገዙ መሆኑን መግለጻቸው፤
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶችን ለመግዛት ከ16 የውጪ አገር የላቦራቶሪ መሳሪያ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ከ2009 ጀምሮ የግዥ ስምምነት ውል የተፈራረመ ቢሆንም እስከ ኦዲቱ ማብቂያ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ያልተከፈተ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2010 በጀት ዓመት አዲስ የግዥ ስራዎችን ማለትም የማህበራዊ ሳይንስ መጻሕፍት፣ የኢንጅነሪንግ መጻሕፍት፣ የላቦራቶሪ መሣሪያዎችና የተማሪዎች መገልገያ ፈርኒቸሮችና ቁሳቁሶች፣ ለተፈጥሮ ሳይንስ የስልጠና መስኮች የሚያስፈልግ የማጣቀሻ መጻሕፍት ግዥ ለመፈፀም ቢታቀድም እስከ ሰኔ 30 2010 ዓ.ም ያልተከናወነ መሆኑ፤ እንዲሁም በ2011 በጀት ዓመት የመጽሐፍት እና የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ግዥዎች የተቋረጡ መሆኑን

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

51. ጉዳዩን በተመለከተ በናሙና ከታዩ ዩኒቨርሲቲዎች ኃላፊዎች ተጠይቀው

- የወራቤ ዩኒቨርሲቲ ኃላፊዎች
  - የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ እቃዎች ባለመኖራቸው የባዮሎጂ፣ የኬሚስትሪ፣ የፊዚክስ እና ሌሎች ቤተ-ሙከራ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በአላጌ ግብርና እና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ፣ በዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ እና በወራቤ ከተማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሚገኙ ቤተ-ሙከራዎች የአገልግሎት ክፍያ በመክፈልና ተማሪዎችን በኪራይ ተሽከርካሪ በማጓጓዝ አገልግሎቱን እያገኙ እንደሆነ በዚህ የተነሳም ለከፍተኛ ወጪ እንደተዳረጉ፣
  - ተማሪዎች መውሰድ ያለባቸውን ኮርሶች በወቅቱ እንዳይወስዱ እንዳደረገ፣ እና

- አላስፈላጊ እንግልት እና ጊዜ እንዳባከነባቸው

የገለፁ መሆኑ፤

- የእንጂባራ ዩኒቨርሲቲ የስራ ኃላፊዎች
  - ዩኒቨርስቲው ስራ የጀመረው በዩኒቨርሲቲው መደበኛ በጀት በጣም አስፈላጊ የሆኑ ግዥዎችን በመፈፀም መሆኑን፣
  - ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በወቅቱ ያደረሳቸው ፍራሽ፣ አልጋና ትራስ፣ የምግብ ቤት ወንበርና ጠረጴዛ በከፊል ብቻ መሆኑን፤ እንዲሁም ዩኒቨርስቲው በራሱ እየገዛም ሆነ ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ እና ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፈርኒቸር በመግዛት ያቀረበ መሆኑን እና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ደግሞ በጎን እያንጠባጠበ ይልክ ስለነበረ የሃብት ብክነት የተከሰተ መሆኑን፣
  - በኦዲት ወቅት በተደረገ ምልከታ በዩኒቨርስቲው ግቢ 1500 የሚደርስ አገልግሎት ላይ ያልዋለ አልጋ ተከማችቶ የተገኘ መሆኑ፣



ምሰል 1. በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ አገልግሎት ላይ ያልዋለ አልጋ በከፊል የሚያሳይ ፎቶ

- የተማሪ ሎከር በወቅቱ ባለመቅረቡ ተማሪዎችን ለስርቆት መዳረጉን እና የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲከሰት ያደረገ መሆኑን፣
- ከዚህ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው እስከ ህዳር 2011 ዓ.ም የArm Chair፣ የቤተ-መጽሐፍ ወንበርና ጠረጴዛ (Circulation desk እና reading table)፣ የመጽሐፍት እንዲሁም የላቦራቶሪ እቃዎች እንዳልተሟሉላቸው

የገለፁ መሆኑ፤

- የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የስራ ኃላፊዎች
  - የማጣቀሻ መጽሐፍት፣ የላቦራቶሪ እቃዎች ኮምፒውተር እና ተዛማጅ እቃዎች በወቅቱ ባለመቅረባቸው እንደተቸገሩ፣
  - ዩኒቨርስቲው የሳይንስ ተማሪዎችን የሚያስተምር ቢሆንም የላቦራቶሪ አገልግሎት ስለሌለ በ2010 ዓ.ም የግብርና እና የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎችን አምቦ ዩኒቨርሲቲ በመውሰድ አገልግሎት ያገኙ መሆኑ እና ይህም ችግር በ2011 ያልተፈታ መሆኑን፤
  - ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚመጡ ዕቃዎች መቸ እንደሚመጡ እና ምን ዓይነት እንደሆኑ ስለማይታወቅ በራሳቸው ለመግዛት የተቸገሩ መሆኑን፣
  - እስከ ህዳር 2011 ዓ.ም 17 ላፕቶፕ እና 15 ዴስክቶፕ ብቻ ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እንደተላከላቸውና ይህም በቂ አለመሆኑን

ገልጸዋል፡፡

52. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው
- በ2008 እና በ2009 በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በኩል በ2010 ሥራ ለሚጀምሩ ዩኒቨርሲቲዎች የበጀት አቅሙ በሚፈቅደው መሰረት አስፈላጊ የሆኑት ዕቃዎች እንዲሟሉ ግዥው እንዲፈፀም ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም ጨረታ ወጥቶ ውሉን እንዲያስተዳድር ከመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የተላከው በጣም ዘግይቶ መሆኑንና ሌተር ኦፍ ክሬዲት ለመክፈት የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ባለመቻሉ የዘገየ መሆኑን፣
- ከዚህም ውጭ ውል ተይዞ በበጀት እጥረት ምክንያት የተፈጥሮ ሣይንስ ላቦራቶሪ መሣሪያዎችን ለመግዛት አለመቻሉን፣

- እንዲሁም ቅድሚያ ሊቀርቡ ለሚገባቸው እቃዎች ብሔራዊ ባንክን በተደጋጋሚ የውጭ ምንዛሪ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው ባለማግኘታቸው ምክንያት ሊዘገይ መቻሉን፣
- የማህበራዊ ሳይንስ መጽሐፍት፣ የኢንጂነሪንግ መጽሐፍትንና መሳሪያዎችን ለመግዛት በእቅድ ቢያዝም በጀት ባለመኖሩና አሁን እየተሰጡ ያሉትን የትምህርት ዓይነቶች እንኳን ሊሸፍን የማይችል በጀት በመሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ተመቻችተው በጀት እየጠበቁ መሆኑን፣
- እንዲሁም ከዚህ ጎን ለጎን ዩኒቨርሲቲዎችም የራሳቸዉን አማራጭ እንዲጠቀሙ ተገልፆላቸዉ እየገዙ መሆኑን፣
- በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ሊገዙ የታሰቡት የተማሪ መገልገያ ዕቃዎች ሲሆኑ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉት በዩኒቨርሲቲዎች በኩል ግዢቸው የሚፈፀም በመሆኑ በዚህ ግዥ ውስጥ እንደማይካተቱ እና በራሳቸው እንዲገዙ በወቅቱ የተገለፀላቸው መሆኑን፣
- የተፈጥሮ ሣይንስ ላብራቶሪ መሣሪያዎች ግዥ ለመፈጸም የሚያስችል ከአስራ አምስት ደርጅቶች ጋር ውል ተይዞ የደረሰን ቢሆንም አጠቃላይ ገንዘቡ ከ400 ሚሊዮን ብር በላይ በመሆኑና አሁን እየተመደበ ባለው የበጀት መጠን ሊገዛ እንደማይችል ተረጋግጦ የበላይ አካል መፍትሄ እንዲፈልግ በተደጋጋሚ ጥያቄ የቀረበ መሆኑን፣
- በዩኒቨርሲቲዎች በራሳቸው የቀረበ ፈርኒቸር ካለ አሰቀድሞ በመግለጽ እንዳይላክላቸው ማድረግ ሲቻል አለመደረጉን እና በዩኒቨርሲቲዎች በኩል ለሚደረጉ ግዥዎች ኃላፊነቱ የዩኒቨርሲቲዎቹ መሆኑን፣
- ሎከር ዘግይቶ መግባቱ ትክክል መሆኑን (ለዘገየበትም ጊዜ በሕጉ መሰረት አቅራቢው ቅጣት ተጥሎበታል) ከዚህ በተጨማሪ ባልቀረቡ ፈርኒቸሮች ላይ አቅራቢው ለማቅረብ ባለመቻሉ በውሉ መሰረት ያስያዘው ፐርፎርማንስ ቦንድ እንዲወረስ መደረጉን፣ በቀጣይ ያልተሟሉ ፈርኒቸሮች ጨረታ ወጥቶ እንዲቀርቡ የሚደረግ መሆኑን፣

በኦዲት ወቅት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

53. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ዩኒቨርሲቲዎቹ በ2010 በጀት አመት ተማሪ ተቀብለው ማስተማር እንደሚጀምሩ አስቀድሞ ይታወቅ የነበረ በመሆኑ የግዥ

ሂደቱን ጎን ለጎን ክትትል በማድረግ ከግንባታው ጋር ማስኬድ ይቻል ስለነበረ እና ዩኒቨርሲቲዎቹ በራሳቸው መግዛት ያለባቸውን እቃዎች በጀት እንዲይዙና እንዲገዙ እንዳልተገለፀላቸው የገለፁ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

54. ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎችና ግብዓቶች በወቅቱ አለመቅረቡ የተማሪዎች መቀበያ ጊዜ እንዲራዘም፣ ተማሪዎች ተገቢውን አገልግሎት እንዳያገኙ እና የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲፈጠር፣ የዩኒቨርሲቲዎች ጊዜ፣ የሰው ኃይል እና ገንዘብ በአላስፈላጊ ሁኔታ እንዲባክን ሊያደርግ እንዲሁም መንግስት የያዘውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል እቅድ ለማሳካት እንቅፋት ይፈጥራል፡፡

## አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑ መረጋገጡን በተመለከተ፣

55. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱም ሆነ ዩኒቨርሲቲዎቹ ሲረከቡ በስፔሲፊኬሽኑ ወይንም በናሙና መሰረት መሆኑን እያረጋገጡ ሊረከቡ ይገባል፡፡

56. ይሁን እንጅ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ቢዘረጋም ተግባራዊ አለማድረጉ ታውቋል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የፈርኒቸር አቅራቢዎች እቃዎቹን ሲያቀርቡ እቃዎቹን ለሚረከቡ ዩኒቨርስቲዎች በቴክኒክ መግለጫው መሰረት እንዲረከቡ ደብዳቤ ከመፃፍ እና የተረከቡበትን ሰነድ ከመቀበል ባለፈ በአካል ሂዶ የማያረጋግጥ እና የማረጋገጡን ስራ ለመስራት ውል የተፈራረመው የአርሲ ዩኒቨርሲቲም ለዩኒቨርሲቲዎች የገቡ የፈርኒቸር እቃዎች በቴክኒክ መግለጫው መሰረት መሆናቸውን ያላረጋገጠ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በቀረቡ ፈርኒቸሮች ላይ የተለያዩ ችግሮች ታይተዋል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በመጋቢት 2010 ዓ.ም በቦንጋ ዩኒቨርስቲ ባደረገው የመስክ ምልከታ ለዩኒቨርሲቲው በቀረቡ የተለያዩ ፈርኒቸሮች ላይ፣

➢ **በተማሪዎች ወንበር/እርም ቼር** (Tablet chair):- **የታዩ ችግሮች፡**

- የወንበሩ አራቱም እግሮች እኩል አለመርገጥ፣
- ብይዱ መልቀቅ እና የተወላገዱ መሆናቸው፣

- የታሰረበት ቡሎን በናሙናው መሰረት አለመሆኑ፣
- የአንዳንዶቹ writing board የተጣመመ መሆኑ፣

➢ **የመመገቢያ እና የምግብ ቤት ወንበሮች (Dining and Lounje chair)**

- የቀረበው ወንበር በሳምፕሉ መሰረት አለመሆን፣ ለምሳሌ የመደገፊያው ውፍረት 10 ሚሊ ሜትር መሆን ሲገባው የቀረበው በ6 ሚሊሜትር መሆኑ፣
- የተወሰኑት ወንበሮች እግራቸው የተጣመመ መሆኑ፣
- የታሰረበት ቡሎን በሳምፕሉ መሰረት አለመሆኑ፣

➢ **ተደራራቢ አልጋ (Double bunk bed)**

- የቀረበው አልጋ እኩል አለመርገጥ፣
- አልጋው በተገቢው መንገድ ሊሰካካ አለመቻሉ እና ተጨማሪ የማስተካከያ ስራ ማስፈለጉ፣ ተሰኪዎቹ በአግባቡ አራቱም ማዕዘን ላይ አለመሰካት፣
- ብይዳቸው መልቀቅ እና መገንጠል፣
- የአልጋው እግር ጎሚኖ አለመኖር፣
- ለፍራሽ ማስቀመጫ ተብሎ የመጣው ፕሌይ ውድ ከአልጋው ሳይገዝ በላይ በመሆኑ የማስተካከያ ስራ መፈለጉ፤

የታዩ የጥራት ችግሮች መሆናቸው መገለጹ፤

57. በኦዲት ወቅት በናሙና በታዩ ዩኒቨርሲቲዎች ዕቃዎች ሲላኩ በቴክኒክ መግለጫ እና በናሙና መሰረት መሆናቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት ስለመኖሩ ተጠይቀው

**የእንጂባራ ዩኒቨርሲቲ ኃላፊዎች**

- አቅራቢዎች ለዩኒቨርሲቲው እቃዎችን ሲያስረክቡ በቴክኒክ መግለጫ (እስፔስፊኬሽን) እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑ የሚረጋገጥበት ስርዓት አለመኖሩን፣
- ገዝቶ የላካቸውን ንብረቶች በቴክኒክ መግለጫው (specification) መሰረት እየቀረቡ መሆኑን ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ክትትል እንዳላደረገና በአካል ተገኝተው የማረጋገጥ ስራ እንዳልሰሩ የገለጹ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለዩኒቨርሲቲው የሚገዛቸውን ዕቃዎች ስፔስፊክሽን እና ናሙና አስቀድሞ ባለመላኩ የሚቀርቡ እቃዎች በትክክለኛው መስፈርት ስለመምጣታቸው ማረጋገጥ እንዳይቻል ማድረጉን የገለፁ መሆኑ፤

- የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የስራ ኃላፊዎች
    - አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ክትትል እንዳላደረገ እና የፈርኒቸር እቃዎችን ስፔስፊኬሽን ቀድመው የላኩ ቢሆንም የሌሎች እቃዎችን እስፔስፊኬሽን የሚልኩት እቃዎቹን አጓጉዞ ለሚያደርስ ትራንስፖርተር መሆኑን ሆኖም እስፔስፊኬሽኑ ቀድሞ ቢመጣ የእቃዎቹን ዓይነትና ብዛት በመለየት ተደጋጋሚ ግኙ እንዳይከሰትም ሆነ ጥራቱን በተሻለ ሁኔታ ለማረጋገጥ ያስችል እንደነበር የገለፁ መሆኑ፤ እንዲሁም
- የወራቤ ዩኒቨርስቲ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው
    - ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የፈርኒቸር ዕቃዎችን ለዩኒቨርስቲው ከመላኩ በፊት ሁለት ባለሙያዎች እንዲላኩ እና የዕቃዎችን ናሙና በማሳየት እና እስፔስፍኬሽን በመስጠት አረጋግጠው እንዲቀበሉ እንዳደረገ፣ ሆኖም ኮምፒውተር ገቢ ሲደረግ ዩኒቨርስቲው በራሱ ባለሙያዎች በማረጋገጥ መቀበሉን፣
    - አቅራቢዎች ዕቃዎችን ለዩኒቨርስርቲው ሲያቀርቡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በአካል ተገኝቶ ክትትል የማያደርግ መሆኑን፤
    - ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የላካቸውን ዕቃዎች ዩኒቨርስቲው መረከቡን እና ገቢ ማድረጉን የገቢ ማድረጊያ ሠነድ ዕቃውን ከአጓጓዘው አካል (transporter) በመቀበል ብቻ የሚያረጋግጥ መሆኑን፤
    - ከዚህ በተጨማሪም ከቀረቡት ዕቃዎች መካከል ጉድለት/ብልሽት ያለባቸውን አልጋና ወንበሮች የተወሰኑትን አቅራቢዎቹ አስተካክለው እንዲመልሱ መደረጉንና አንዳንድ ፈርኒቸሮችን በአጣዳፊ ሰዓት የመጡ በመሆኑ ዩኒቨርስቲው በራሱ ወጪ አስተካክሎ ጥቅም ላይ ሲያውል ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉን የገለፁ መሆኑ፤
- ከዚህ በተጨማሪም የብረት እና የሲሚንቶን አቅርቦት በተመለከተ በናሙና በታዩ በወራቤ ዩኒቨርሲቲ፣ በእንጂባራ ዩኒቨርሲቲ እና በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ በሚገኙ ግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክቶች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ብረት እና ሲሚንቶ በሚልክበት ወቅት የተላከውን የግብዓት ዓይነትና ብዛት የሚገልጽ ሰነድ እቃውን ከሚያጓጉዘው ሾፌር በመቀበል የመጣውን ግብዓት ከሰነዱ ጋር ተመሳክሮ የገቢ ሰነድ ተቆርጦ እንደሚመለስ ሆኖም የአርማታ ብረት አስቀድሞ በተዘጋጀ ደረጃ (grade) መሰረት መሆኑ እንደማይረጋገጥ ገልፀዋል፡፡

58. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው

- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በኩል ለሚገዙ ዕቃዎች ውል ፈጽሞ እስፔስፊኬሽንና የቴክኒክ ግምገማውን ሊሰራ ስምምነት ያደረገው ዩኒቨርሲቲ በናሙና ዩኒቨርሲቲዎች ተገኝቶ የቀረቡ ዕቃዎች በስፔስፊኬሽኑ መሰረት መሆን አለመሆኑን አረጋግጦ ሪፖርቱን አቅርቦ ለኦዲት ቡድኑ የሪፖርቱ ኮፒ መሰጠቱን ይሁን እንጂ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ተገኝቶ ለማረጋገጥ ባለመቻሉ ከየዩኒቨርሲቲዎቹ ባለሙያዎችን አሰባስቦ ከሚረከቡት ዕቃ ጋር ማስተዋወቅና መለየት እንዲችሉ ስልጠና መሰጠቱን፣
- የቀረቡት ፈርኒቸር ከስፔስፊኬሽኑ ውጭ ቀርበው ተቀብለናል ለሚለው በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ከእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ ሁለት ሁለት ባለሙያዎችን አስመጥተን በናሙናነት የቀረቡትን ከእያንዳንዱ ከፈርኒቸር ጋር አስተዋውቀን ዝርዝር ስፔስፊኬሽኑን በመስጠት ልዩ ትኩረት ሊያደርጉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች በማሳወቅ የተመለሱ ቢሆንም ከስፔስፊኬሽኑ ውጭ ቀርበው አቅራቢው ድርጅት በራሱ ወጭ መልሶ አስተካክሎ እንዲያቀርብ የተደረጉባቸው ዩኒቨርሲቲዎች አሉ፣ ከዚህ ውጭ ገቢ ተደርገው ከሆነ ኃላፊነቱ ገቢ ያደረገው ዩኒቨርሲቲ እንጂ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አለመሆኑን፣
- በእንጂባራ፣ በሰላሌ እና በወራቤ ዩኒቨርሲቲዎች በቀረቡ እቃዎች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ክትትል አላደረገም ለተባለው በውሉ መሰረት በናሙና ዩኒቨርሲቲዎች በመገኘት እያንዳንዱን ፈርኒቸርና የምግብ ቤት ዕቃዎችን በማየት በስፔስፊኬሽኑ መሰረት የቀረቡትን ሲቀበል ያልሆኑትን ተቀባይነት አለመስጠቱን እና በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ማየት አስፈላጊ ባለመሆኑ አለመታየቱን፣
- የቴክኒክ መግለጫ/ እስፔስፊኬሽንን በተመለከተ ዕቃዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት አለመግባታቸውን በመለየት የተፈለጉት ዕቃዎች በሙሉ መቅረባቸውን አረጋግጦ ለስርጭት ዝግጁ ሲሆኑ ለዩኒቨርሲቲዎቹ ከነሙሉ ስፔስፊኬሽኑ በተረጋገጠ ሰነድ አስደግፎ እንደሚልክ፣ ሁሉም ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተባቸው ዕቃዎች ላይቀርቡ ስለሚችሉ ይህን ሁኔታ ሳንለይ ስፔስፊኬሽን መላኩ ችግር ስላለው አለመደረጉን፣

- ብረትን በተመለከተ በአቅራቢ መረጣ ውድድር ጊዜ በፍተሻ ተረጋግጦ አቅራቢው እንደሚመረጥ እና ቴክኒካል ግምገማ ወደ ሳይቱ ከመሄዱ በፊት እንደሚደረግ ከዚያ በኋላ የግንባታ ተቋራጩ የቀረበለትን ብረት አረጋግጦ የሚቀበል መሆኑን

በኦዲት ወቅት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ ምላሽ ገልፀዋል፡፡

59. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ያሉ ቢሆንም

- በእስፔስፊኬሽን መሰረት እቃዎች መግባታቸውን ለማረጋገጥ እንደ አማካሪ ውል የተዋዋለው የአርሲ ዩኒቨርሲቲ አቀረበው የተባለው ሪፖርት በየትኛው ዩኒቨርሲቲ የገቡ ፈርኒቸሮችን እንዳረጋገጠ የማይገልጽ በመሆኑ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ጊዜ በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ብቻ መሰራቱ የተገለፀ በመሆኑ እና ሪፖርቱም ተሰራ የተባለው የፈርኒቸር እቃዎቹ ከቀረቡ ከአንድ ዓመት አካባቢ በኋላ በመሆኑ፣
- በትምህርት ሚኒስቴር (አሁን የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር) በኩል ከእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ ሁለት ሁለት ባለሙያዎችን አስመጥተን በናሙናነት የቀረቡትን ከእያንዳንዱ ፈርኒቸር አይነት ጋር የማስተዋወቅ ስልጥና ተሰጥቷል ለተባለው ባለሙያዎቹ መሰልጠናቸው ብቻ እቃዎቹ ገቢ ሲደረጉ በቴክኒክ መግለጫው እና በናሙና መሰረት መሆናቸው ይረጋገጣል የሚለውን ስለማያሳይ እና ውል የተዋዋለው ዩኒቨርሲቲም እቃዎች ሲቀርቡ የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፣
- በተወሰኑ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በናሙና መርጦ የማረጋገጥ ስራ ሰርቷል የተባለው በኦዲት ወቅት የኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ ባደረገባቸው ሶስቱ ዩኒቨርሲቲዎች እቃዎች ሲቀርቡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የማረጋገጥ ስራ ያልሰራ መሆኑን የገለፁ በመሆኑ፣
- የአርማታ ብረትን በተመለከተ አቅራቢ ለማወዳደር በሚከናወን ጨረታ ጊዜ እና ወደሳይት ከመጓጓዙ በፊት በምርት ሂደት የሚደረግ የጥራት ግምገማ ትክክለኛ ብረት ገቢ ለመሆኑ ማረጋገጫ ስለማይሆን

የተሰጠውን መልስ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል አያስችልም፡፡

60. በግዥ የሚቀርቡ እቃዎች በቴክኒክ መግለጫ እና በናሙና መሰረት መሆናቸው ካልተረጋገጠ ከጥራት በታች የሆኑ እቃዎች እንዲገቡ፣ ለተጨማሪ ወጪ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር በር ሊከፍት፣ እንዲሁም መንግስት ካወጣው ገንዘብ ማግኘት ያለበትን ጥቅም እንዳያገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የተገዙ ዕቃዎች በወቅቱ ተሰራጭተው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የተደረገ ስለመሆኑ፣**

61. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተገዙ ዕቃዎችን ለተጠቃሚ ዩኒቨርሲቲዎች በወቅቱ ሊያሰራጭ እና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

62. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በዩኒቨርስቲዎች የምግብ ማዘጋጃ፣ ማብሰያ እና ማቅረቢያ እቃዎችና ጄነሬተር ግዥ ፈጽሞ በጥቅምት 2011 ዓ.ም ወደ 11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የላከ ቢሆንም ከዩኒቨርስቲዎቹ ጋር እርክክብ ያልተፈፀመ እና እቃዎቹ አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆኑ ታውቋል፡፡



ምስል 2. በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ እርክክብ ያልተፈፀመባቸው እና አገልግሎት ላይ ያልዋሉ የምግብ ቤት እቃዎችን በከፊል የሚያሳይ ፎቶ



ምስል 3. በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ እርክክብ ያልተፈፀመባቸው እና አገልግሎት ላይ ያልዋሉ የምግብ ቤት እቃዎችን በከፊል የሚያሳይ ፎቶ

63. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልሱ አብዛኛው የቀረቡት ዕቃዎች ትልልቅ ማሽኖች በመሆናቸው እስከ ምግብ ማብሰያ

ክፍሎች ድረስ የሚያስገባ መንገድ ባለመኖሩና የተሰራው በር ሊያስገባ ባለመቻሉ፣ ይህ እስኪሟላ ድረስ መዘግየቱን፣ ጄኔሬተርን በተመለከተ በኬብል ችግርና የጀኔሬተሩ ማስቀመጫ ባለመገንባቱ፣ እንዲሁም ከዋናው ዲስትሪቢዩሽን ቦርድ ጋር ለማያያዝ አማካሪዎች ባለመፍቀዳቸው ይህ ሁኔታ እስኪሟላ ድረስ ሊዘገይ እንደቻለ፣ ሆኖም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ትዕዛዝ በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ስራው መጀመሩን ገልፀዋል፡፡

64. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ከቀረቡት እቃዎች መካከል በመጠን አነስተኛ ማሽኖችና ዕቃዎች ሆነው አገልግሎት ላይ ያልዋሉ በመኖራቸው፣ የተሰሩ በሮች ማሽኖቹን አያስገቡም የተባለውም ህንፃዎቹ ሲገነቡ የሚገቡባቸው ማሽኖች ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ እንዳለ ለመቀበል አያስችልም፡፡

65. የተገዙ እቃዎች በወቅቱ አገልግሎት ላይ ካልዋሉ ለእርጅና፣ ለብልሽት፣ ለስርቆትና ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርጉ እንዲሁም ተጠቃሚ ዩኒቨርሲቲዎች ተገቢውን አገልግሎት እንዳይሰጡ ያደርጋል፡፡

## ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግዥ የተመደበለትን በጀት በወቅቱና በአግባቡ ስራ ላይ ያዋለ ስለመሆኑ፣

66. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግዥ የተመደበለትን በጀት የመንግስት የግዥ ስርዓትን ጠብቆ በወቅቱና በአግባቡ ስራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

67. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግንባታ የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች አይነትና ብዛት በስራ ቅደም ተከተል በትክክል በመለየት መጥኖ ባለመግዛቱ የባለ 10 የአርማታ ብረት ለግንባታ ከሚያስፈልገው ብዛት በላይ በየግንባታ ሳይቶች ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ተከማችቶ መገኘቱ፤ ለምሳሌ በናሙና ከታዩ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ በህዳር 2011 ዓ.ም ለሳይት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ የተከማቸ በወቅቱ በተገዛበት ዋጋ መሰረት ብር 1,639,848.00 አካባቢ የሚደርስ 12,263 ቤርጋ ብረት የተከማቸ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

68. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የግንባታው ሂደት በበጀት እጥረት ምክንያት እንደታሰበው ባለመከናወኑ የተጠቀሰዉ የብረት ክምችት ሊከሰት መቻሉን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

69. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተመደበለትን በጀት በሚሰራው ስራ ልክ እና በአግባቡ ካልተጠቀመ ወቅታዊ እና በጣም አስፈላጊ ግዥዎች እንዳይፈፀሙ፣ በእቅድ የተያዙ ተግባራት መፈፀም እንዳይቻል እንዲሁም መ/ቤቱ መስጠት ያለበትን አገልግሎት በአግባቡ እንዳይሰጥ እንቅፋት ሊፈጥር ይችላል፡፡

## የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የአቅም ግንባታ ሥራን በተመለከተ

70. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር የስራ ተግባራትን ለሚያከናውኑ ሰራተኞች የፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁ.649/2001፣ የአፈፃፀም መመሪያውን፣ የግዥ ማንዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና ሌሎች ተገቢ ቅፆች ይዘት እና አጠቃቀም እንዲያውቁ ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና ሊሰጣቸው እና የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን ለመፈፀም በቂ ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

71. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የአቅም ግንባታ ስራን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ

- የግዥና ንብረት አስተዳደር የስራ ተግባራትን ለሚያከናውኑ ሰራተኞች የፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁ.649/2001፣ የአፈፃፀም መመሪያዎችን እና ሌሎች ተገቢ ቅፆች ይዘት እና አጠቃቀም እንዲያውቁ ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና ያልተሰጠ መሆኑ፤
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከ2008-2010 በጀት ዓመታት የሠራተኛውን የቴክኖሎጂና የመፈፀም የአቅም ክፍተት በመለየት በተከታታይ ስልጠና አቅሙን ለማጎልበት በእቅድ ቢ.ይዝም ያላከናወነ መሆኑ፤
- በኦዲት ወቅት በናሙና በታዩ በሶስት ዩኒቨርስቲዎች በሚገኙ የግንባታ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች የሚሰሩ የሎጅስቲክስ እና ንብረት አስተዳደር ባለሙያዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ምንም ዓይነት ስልጠና ተሰጥቷቸው እንደማያውቅ ገልፀዋል፡፡

72. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሰራተኞች መጀመሪያ ወደ ስራ ሲገቡ ስልጠና መሰጠቱን፣ በየሳይቱ ለመስክ ስራ ሲወጣ ተገቢው ምክርና ድጋፍ እንደሚደረግ በቀጣይ ግን በእቅድ ተይዞ ሥልጠና እንዲያገኙ እንደሚሰሩ፣ የሰራተኞች ስልጠና ወጥ በሆነ በመስሪያ ቤቱ አጠቃላይ የስልጠና መርሀ ግብር የሚፈጸም በመሆኑ የተናጠል ስልጠና እንደማይሰጥ ገልፀዋል፡፡

73. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ሰራተኞች ወደስራ ሲገቡ ስልጠና ተሰጥቷል የተባለው የስራ ማስተዋወቅ/ኦሬንቴሽን እንጂ ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች ጋር በተገናኘ የተሰጠ ስልጠና ባለመኖሩ፣ በቀጣይ በእቅድ ላይ ተመስርተው ስልጠና እንደሚሰጡ እና የተናጠል ስልጠና እንደማይሰጥ የተገለጸው እርስ በእርሱ የሚጋጭ ሃሳብ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

74. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ባለሙያዎች አስፈላጊው ስልጠና ካልተሰጣቸው የሚሰሩትን ስራ ህግና ደንብ ተከትለው በጥንቃቄ መስራት እንዳይችሉ፣ ለመታለል እና ለመጭበርበር

ሊዳረጉ፣ እንዲሁም የባለሙያዎችን የመፈፀም ክህሎት ሊያሳጣና አጠቃላይ የስራ አፈፃፀም እንዲቀንስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የፕሮጀክቱ ንብረት በሚገባ የተመዘገበ እና ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግለት ስለመሆኑ፣

75. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ፕሮጀክት ጽ/ቤት ንብረት በሚገባ የተመዘገበ እና ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግለት ሊሆን ይገባል፡፡

76. ይሁን እንጂ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታ ግብዓቶች አስተዳደርን በተመለከተ

- የግንባታ ግብዓቶች ወጥነት ባለው መልኩ የሚመዘገቡበት አሰራር አለመኖሩ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከ2008 ጀምሮ ለግንባታ የተገዙ ግብዓቶች ብዛት፣ ግንባታ ላይ የዋሉ የሲሚንቶ እና የአርማታ ብረቶች፣ እንዲሁም በየግንባታ ሳይቱ የተከማቹ የአርማታ ብረቶች መዝገብ በተሟላ መልኩ አለመኖሩ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በነሀሴ 2009 ዓ.ም በቦንጋ ዩኒቨርስቲ ባደረገው የመስክ ምልከታ ሲሚንቶን በተመለከተ ከፍተኛ ብክነት መታየቱ፤ ዘላለም በተባለ ስራ ተቋራጭ ሳይት ላይ ፕሪካስት ለማምረት የተዘጋጀ ባለ 6 ቁጥር እስታፋ ብረት ጥቅም ላይ ሳይውል ተጠላልፎ የተቀመጠ መሆኑ፣ የአርማታ ብረት የተከማቸበት ቦታ በአግባቡ ያልተከለለ እና በሳር የተዋጠ መሆኑ፤
- በነሀሴ 2008 ዓ.ም በወራቤ ዩኒቨርሲቲ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ባደረገው የመስክ ምልከታ የአርማታ ብረት የተከማቸበት ቦታ አጥር አለመኖሩ፤ ለህንፃ ግንባታ የተገዛው ሲሚንቶ የተከማቸው በግለሰብ የኪራይ መጋዘን መሆኑ እና ከመጋዘን አከራዩ ፋብሪካ ውስጥ በመሆኑ ያለው ጥበቃ የፋብሪካው እንጂ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ያልነበረ መሆኑ፤ እንዲሁም በነሀሴ 2009 ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ባደረገው የመስክ ምልከታ ፒራሚድ በተባለ ስራ ተቋራጭ ሳይት ብዛት ያለው ባለ 14 ቁጥር ከ3 ሜትር በላይ እርዝመት ያለው ቁርጥራጭ ብረት ተከማችቶ መገኘቱ፤
- በጂንካ ዩኒቨርስቲ በየካቲት 2010 ዓ.ም ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን አጠቃቀም በተመለከተ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተደረገ የመስክ ምልከታ የሚከተሉት ችግሮች የታዩ መሆኑ፣
    - ለተቋራጮች የግንባታ ግብዓት በሞዴል 22 ወጪ ሲደረግ በአነሰ ዋጋ ወጪ ማድረግ እና የተቋራጩን ስም በትክክል አለመፃፍ፣
    - ከተቋራጮች ተመላሽ መሆን የነበረበት አርማታ ብረት ተመላሽ አለመሆን፣

- በብክነት ሊያዙ የማይችሉ ቁመታቸው ከ2 ሜትር እስከ 10 ሜትር የሚሆኑ ብረቶች በየስራ ተቋራጩ እጅ የሚገኙ መሆናቸው፣
- 631 ኩንታል ሲሚንቶ ለብልሽት እና ለብክነት መዳረጉ፣
- የአርማታ ብረቱ ከዩኒቨርስቲው ግቢ ውጪ መከማቸቱ፣
- የዩኒቨርስቲው ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ቢሮ ከዩኒቨርስቲው ግቢ ውጭ በመሆኑ ለቁጥጥር አመቺ አለመሆን፣

- በቀብሪ ደሃር ዩኒቨርስቲ በሐምሌ 2009 ዓ.ም ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን አጠቃቀም በተመለከተ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተደረገ የመስክ ምልከታ የሚከተሉት ችግሮች የታዩ መሆኑ፣
  - የሲሚንቶና ብረት አወጣጥን የተመለከቱ መረጃዎች በአግባቡ ያልተያዙ መሆኑ፣
  - የአርማታ ብረት በሰንሰለት ያልታሰረና ለቁጥጥር አስጊ መሆኑ፣
  - በዩኒቨርሲቲው በሚገኘው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ንብረት ገቢ ሰነድ 0044017 ላይ 200 ኩንታል ሲሚንቶ የተቀረጠ ቢሆንም ሲሚንቶ ከፋብሪካው ወጪ ያልሆነ እና ወደ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱም ለክፍያ ያልመጣ መሆኑ፣
  - የአርማታ ብረት ከማዕከል (ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ) የተላከው 14,938.59 ኩንታል ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው በሚገኘው የግንባታ ጽ/ቤት የንብረት ገቢ ሰነድ ላይ ተመዝግቦ የሚገኘው 15,988.59 ኩንታል መሆኑ፣ በዚህም ምክንያት 1,050 ኩንታል ልዩነት ማሳየቱ፣
  - 40 ኩንታል የሚሆን ሲሚንቶ በአያያዝ ጉድለት ለብልሽት መዳረጉ፣
  - ሰነድ አያያዝን በተመለከተ ምንም ዓይነት ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ የሌለ መሆኑ፣

- የንብረት አጠባበቅ እና አያያዝን በተመለከተ ከ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ሳይቶች በናሙና ከታዩ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ለእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት በቀረበ ቃለ መጠይቅ የአርማታ ብረት ማከማቻ ቦታ እና አጥር እንዲሰራላቸው ፕሮጀክት ጽ/ቤቱን በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ምላሽ አለማግኘታቸውና በዚህ ምክንያት የአርማታ ብረት አላግባብ መሬት ላይ እንዲከማች እና በዝናብ ጊዜ ተሸከርካሪ የማያስገባ በመሆኑ የአርማታ ብረት አቅራቢዎችም ሆነ ስራ ተቋራጮች አገልግሎት ለማግኘት የተቸገሩ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡



**ምስል 4.** በእንጂባራ ዩኒቨርሲቲ የብረት አቀማመጥን በከፊል የሚያሳይ ፎቶ



**ምስል 5.** በወራቤ ዩኒቨርሲቲ የብረት አቀማመጥን በከፊል የሚያሳይ ፎቶ

77. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው

- በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የተገለፀውን ብረት በተመለከተ ብረቱ ተቋራጩ ተረክቦ የወሰደው በመሆኑ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱን የሚመለከት አለመሆኑን፣ ለሲሚንቶም ሆነ ለብረቱ ዋጋው በምህንድስና ክፍል ተሰልቶ ዘላለም ከተባለው ተቋራጭ ክፍያ ላይ እንዲቀነስ እንደሚደረግ፣
- ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ማቴሪያልን ካሉአቸው መጋዘኖች በአንዱ እንዲያስቀምጡና ጥበቃውን በዩኒቨርሲቲው ስር እንዲሆን ቢደረግም የወራቤ ዩኒቨርሲቲ ሊያደርግ ባለመቻሉ ተደጋጋሚ ማሳሰቢያ የተሰጠው መሆኑን፣

- በስራ ተቋራጮች እጅ የሚገኙ ቁርጥራጭ ብረቶችን በተመለከተ የብረቱ ዋጋ ኮንትራክተሩ ላይ የተቀነሰ ሲሆን ብረቱን ይዞ ለመውጣት የኘት ዋጋ በመንግስት በመሸፈኑና ሙሉ በሙሉ የኮንትራክተሩ ባለመሆኑ ባለበት ሁኔታ መቆየቱን እና መፍትሄ ለመስጠት እየተሰራበት እንደሚገኝ፣
- ሲሚንቶ በየሳይቱ በሚቀርበው የፍላጎት ጥያቄ መሰረት እንደሚሰራጭ ከዚህ ውጭ ተቀምጦ ለብልሽት የተዳረገ ካለ በምን ምክንያት እንደተከሰተ መጣራት ስለሚፈልግ ጉዳዩን በትኩረት እንደሚሰሩበት፣
- በቀብሪደሃር ዩኒቨርሲቲ የሲሚንቶና ብረት አወጣጥን በተመለከተ አወጣጡ በመንግስት የዕቃዎች ገቢና ወጭ ሰነድ እንጂ በሌላ ሁኔታ መሆን እንደሌለበት በምልከታ ወቅት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የገለፁ መሆኑን፣
- የአርማታ ብረት ማሰሪያ ሰንሰለት በወቅቱ ተገዝቶ የተላከ መሆኑን ይሁን አንጂ በሰንሰለቱ ያልተጠቀሙ በመሆኑ እንዲስተካከልም ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያ መስጠቱን በቀጣይም ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን፣
- በቀብሪደሀር ዩኒቨርሲቲ በገቢ ሰነድ የተቀረጠው 200 ኩንታል ሲሚንቶ በወቅቱ አየር ባየር የማጭበርበር ዘዴ መሆኑ ታውቆ ገቢ አደረገ በተባለው ግለሰብ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ቢደረግም እስካሁን ተሰውሮ አለመገኘቱን እና በማጭበርበር ቀረበ ለተባለው ሲሚንቶው ሂሳቡም ያልተከፈለ መሆኑን፣
- በቀብሪደሀር ዩኒቨርሲቲ ከማዕከል በተላከው እና በገቢ ሰነድ ታየ በተባለው ልዩነት በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የገቢና ወጭ ሰነድ እንዳልታየ ሆኖም ሁኔታውን ልዩ ትኩረት ሰጥተው ውጤቱን ለማየት በሂደት እንደሚገኙ፣
- የስቶክ ካርድ እና ቢንካርድ አጠቃቀምን በተመለከተ አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች መጠቀም ቢጀምሩም ወጥ ባለመሆኑ ወደፊት የልምድ ልውውጥ በማድረግ የማስተካከያ ስራ እንደሚሰሩ፣
- በእንጂባራ ዩኒቨርሲቲ የብረት ማስቀመጫ ቆጥ ተሰርቶ አገልግሎት ላይ የነበረ ቢሆንም ከጊዜ በኋላ በመበስበሱ በዩኒቨርሲቲው በኩል በቀይ አሸዋ መሬቱ ተደልድሎ እንዲሰራ የተገለፀላቸው መሆኑን

በኦዲት ወቅት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ በተሰጠ ምላሽ ገልፀዋል፡፡

78. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት በሚገባ ተመዝግቦ ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ካልተደረገለት ለስርቆት፣ ለብልሽት፣ ለእርጅና፣ ለምዝበራ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ይሆናል፡፡

**የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ እና ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ክትትል የተደረገ ስለመሆኑ፣**

79. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ እና ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ መደበኛ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

80. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ11ዱ ዩኒቨርሲቲዎች በሚገኙ የግንባታ ሳይቶች ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ እና ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ አልፎ አልፎ የተከታተለ ቢሆንም

- ክትትሉ መደበኛ አለመሆኑ እና ክትትል ባደረገባቸው የግንባታ ሳይቶች ግብረ-መልስ ያልሰጠ መሆኑ፣
- በሚያዚያ 2009 ዓ.ም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በቀብሪደሀር ዩኒቨርሲቲ የንብረት አስተዳደር ክትትል ሲያደርግ የተለያዩ ችግሮች ቢያገኝም በድጋሚ በጥር 2010 ዓ.ም በዩኒቨርስቲው የመስክ ክትትል ሲደረግ ክትትሉ ህንፃዎች ያሉበትን ደረጃ በፎቶ ከማሳየት ባለፈ የግንባታ ግብዓት አያያዝ እና አጠቃቀምን በተመለከተ እንዲሁም ቀድሞ በተደረገው ምልከታ የታዩ ችግሮች ስለመቀረፋቸው የተገለፀ ነገር አለመኖሩን

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

81. ይህን በተመለከተ በናሙና በታዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚገኙ የግንባታ ማስተባበሪያ ቅርንጫ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መደበኛ ባይሆንም አልፎ አልፎ ክትትል እንደሚያደርግ እና ክትትል በሚያደርግበት ጊዜም ግብረመልስ እንዳልሰጣቸው ገልፀዋል፡፡

82. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ ተጠይቀው ሲመልሱ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሎጂስቲክስ እና ግዥ ባለሙያ ከአንዴም ሁለቴ የመስክ ምልከታ ተደርጎ አስፈላጊው ክትትል፣ ድጋፍና ማስተካከያ መደረጉን፣ ክፍተቶች ካሉ ክትትልና እርማቱ ቀጣይ እንደሚሆን፣ በተጨማሪም በየሳይቱ የታዩትን ግምገማዎች ወዲያውኑ በአካል በግብረ መልስነት የሚሰጥና እርምት መወሰድ የሚገባቸውን ወዲያውኑ እንዲታረሙ ከማድረግ ውጭ በጽሁፍ የሚሰጥ ነገር አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

83. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ መደበኛ ክትትል ካላደረገ እና ለሰራቸው የክትትል ሪፖርቶች ግብረ-መልስ ካልሰጠ ንብረት አላግባብ

ሊባክን እና በንብረት አያያዝ ዙሪያ ያሉ ችግሮች በወቅቱ እንዳይቀረፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ የሚካሄድበት ስለመሆኑ እና የንብረት አስተዳደር ሰራተኞች መ/ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት የሚደረግ ስለመሆኑ፣**

84. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ ሊካሄድበት ይገባል፡፡ እንዲሁም የንብረት አስተዳደር ሰራተኞች መ/ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት ሊደረጉ ይገባል፡፡

85. ይሁን እንጂ

- በ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሲሚንቶ እና የአርማታ ብረቶች ዓመታዊ ቆጠራ ያልተደረገባቸው መሆኑ፣
- በናሙና በታዩ ሶስት ዩኒቨርሲቲዎች ለሚገኙ የግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ሲሚንቶ በመጋዘን ብዙ ጊዜ እንደማይቀመጥ እና የአርማታ ብረት ግን ከ2008 ጀምሮ የተከማቸ ቢኖርም ቆጠራ ተደርጎበት እንደማያውቅ የገለፁ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የንብረት አስተዳዳር ሰራተኞች ፕሮጀክት ጽ/ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት የሚደረጉበትን አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ከ27/02/2010 ጀምሮ ውሉ የተቋረጠ ቢሆንም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የመስክ ክትትል እስካደረገበት 11/7/2010 ድረስ ንብረት ወጪ እያደረገ የነበረ መሆኑን

በኦዲት ወቅት በተደረገ የመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

86. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው

- ሲሚንቶ በየሳይቱ በሚቀርብ የፍላጎት ጥያቄ መሰረት የሚሰራጭ በመሆኑ ክምችት ስለማይኖር ቆጠራ እንዳልተደረገ እና ብረትን በተመለከተ ቆጠራው ከፍተኛ ወጪ ስለሚያስወጣ ለማስቆጠር አለመቻሉን ሆኖም ወደፊት ብክነት እንዳይከሰትና ችግሮቹን ለመቅረፍ እየሰሩ መሆኑን፣

- የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲትን በተመለከተ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተዘረጋ ስርዓት ባይኖርም በውስጥ ኦዲት ቁጥጥር እንዲደረግ እንደሚሰሩ፣
- በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የተጠቀሰውን ግለሰብ በተመለከተ ግለሰቡ ሌላ ሰዉ ወክሎ ስራው እንዳይቆም ተደርጎ ሲሰራ ቆይቶ የነበረና በኋላ ደብዳቤ ተጽፎ ተያገዞ ባለበት ብረቱም ሆነ ሲሚንቶው ተቆጥሮ እርክክብ ተፈጽሞ መሰናበቱን

በኦዲት ወቅት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ምላሽ ገልፀዋል፡፡

87. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ

- ለቆጠራ ያስፈልጋል የተባለው ወጪ ተጠንቶ የቀረበበት አግባብ ባለመኖሩ፣
- የውስጥ ኦዲት ይቆጣጠራል የተባለው በኦዲት ወቅት በናሙና በታዩ ሳይቶች ክትትል እንዳልተደረገ የሚታወቅ በመሆኑ እና የስራ ክፍሉም ክትትል ስለማድረጉ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣
- እንዲሁም በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የለቀቀ ባለሙያ ሌላ ሰው ወክሎ ሲያሰራ ነበር ተብሎ የተመለሰው የለቀቀው ባለሙያ እርክክብ ሳይፈጽም ሌላ ግለሰብ ማሰራት ለንብረቱ ተጠያቂ ባለቤት የሚያሳጣ እና መሰረታዊ የውስጥ ቁጥጥር ስህተት በመሆኑ

የተሰጠውን ምላሽ መቀበል አያስችልም፡፡

88. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የንብረት ቆጠራ አለማድረጉ የመ/ቤቱ ሀብትና ንብረት በትክክል እንዳይታወቅና ለሚመለከተው አካል አስፈላጊ የውሳኔ ሃሳብ ለማስተላለፍ የሚያስችል መረጃ እንዳይሰጥ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የንብረት አስተዳደር ሰራተኞች መ/ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት ካልተደረገ ሰራተኞቹ በቆይታቸው በተረከቡት እና ወጪ ባደረጉት ንብረት ተጠያቂ እንዳይሆኑ በማድረግ ለስርቆት፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ይዳርጋል፡፡

## የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ የሚወገድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ የተደረገ ስለመሆኑ፣

89. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ የሚወገድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ

- ንብረት አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ የሚወገድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- ከተቋራጮች ተመላሽ የሚደረጉ ቁርጥራጭ የአርማታ ብረቶች መረከቢያ የሚሆን ሚዛን አለመኖሩ፣
- በናሙና በታዩ የዩኒቨርስቲ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለተቋራጮች ወጪ ከተደረጉ የአርማታ ብረቶች የሚተርፉ ቁርጥራጭ ብረቶች ቢኖሩም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በምን መልኩ እንደሚቀበል የተላለፈ መመሪያም ሆነ አሰራር ባለመኖሩ ተመላሽ እንዳልሆኑ በዚህ የተነሳም ቁርጥራጭ ብረቶች ለስርቆት የተዳረጉበት ሁኔታ እንዳለ እና የተቋራጮች ተደጋጋሚ ቅሬታ እንዳስከተለ የገለፁ መሆኑን

በኦዲት ወቅት በተደረገ የመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

91. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የንብረት አወጋገድን በተመለከተ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ እንደ ዋና አጀንዳ ወስዶ እየተወያየበት እንደሚገኝ እና የቁርጥራጭ ብረቶች ጉዳይ እስካሁን በሂደት ላይ ያለ በመሆኑ ውሳኔ ላይ ሲደረስ መፍትሄ እንደሚያገኝ በኦዲት ወቅት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ገልፀዋል፡፡

92. አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ህግና ስርዓትን ጠብቀው የሚወገዱበት አሰራር ካልተዘረጋ ንብረቶቹ ለስርቆትና ለብልሽት ከመዳረጋቸው በተጨማሪ የንብረት ይወገድልኝ ጥያቄ ለሚያነሱ ተቋራጮች ተደጋጋሚ ቅሬታ በማስነሳት የመልካም አስተዳደር ችግር ይፈጥራሉ፡፡

## ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፣

93. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ዓላማውን ለማሳካት ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት እና ከአቅራቢዎች ጋር በቅንጅት ሊሰራ እና በግዥ ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ የመወያያ መድረኮችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

94. ይሁን እንጂ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ

- ከአቅራቢዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በግዥ ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ መደበኛ የመወያያ መድረኮች ያልተዘጋጁና ያልተቀረፉ ችግሮቹ ያሉ መሆኑ፣

- ለዩኒቨርሲቲዎች አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ግብዓቶች አቅርቦትና በተከሰቱ ችግሮች ዙሪያ ውይይት ማድረግን በተመለከተ በናሙና በታዩ ዩኒቨርሲቲዎች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በመደበኛነት ለዚህ ዓላማ ተብሎ የተዘጋጁ የውይይት መድረኮች ባይኖሩም አልፎ አልፎ በሚደረጉ የውይይት መድረኮች ላይ የግብዓት አቅርቦት እጥረት እና ችግሮች እንደሚነሱ የገለፁ ሲሆን በዚህ ዙሪያ መደበኛ የውይይት መድረኮች አለመኖራቸው ችግሮች በወቅቱ እንዳይፈቱ፣ ዩኒቨርሲቲዎች ማተኮር ባለባቸው እስትራቴጅክ ጉዳዮች ትኩረት ማድረግ እንዳይችሉ እና በግዥ በኩል ያልተቀረፉ ችግሮች ዩኒቨርሲቲዎችን ለአላስፈላጊ ወጪ እንደዳረጋቸው የገለፁ መሆኑ

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

95. ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ወቅት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ከህንፃ ስራ አማካሪዎችና ከተቋራጮች ጋር እንደ አስፈላጊነቱ ውይይት እንደሚደረግ፣ ሆኖም ከትምህርት ግብዓቶች እና ከግንባታ ግብዓት አቅራቢዎች ጋር መደበኛ የውይይት መድረኮች አለመኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

96. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ካልሰራ እንዲሁም መደበኛ የመወያያ መድረኮች ካልተፈጠሩ ከግዥ እና ንብረት አስተዳደር ጋር በተገናኘ የሚከሰቱ ችግሮችን በወቅቱ ለመፍታት አዳጋች ሊያደርግና እቅዶችን በተቀላጠፈ መልኩ ማከናወን እንዳይቻል ሊያደርግ ይችላል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ (Conclusion)

97. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ስራ ለመጀመር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ግዥዎች የሦስት ዓመታት እቅድ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሲሚንቶ እና የአርማታ ብረት ግዥዎችን ከመፈፀሙ በፊት የግብዓቶቹን ዓይነትና ብዛት በዓመታዊ እቅዶቹ ለይቶ አለማስቀመጡ እና ለፈፀማቸው ግዥዎች የገበያ ጥናት ያላደረገ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለ11ዱ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገዙ እቃዎችን የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫውንም ሆነ የግዥ ውሉን አስቀድሞ አለመላኩ፣
- እንዲሁም የተፈጥሮ ሳይንስ መጽሐፍት ግዥ እና የፈርኒቸርና የምግብ ቤት እቃዎች ግዥዎችን የማማከር ስራ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ ፈቃድ ሳይኖራቸው የተሰጠ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከፍተኛ ግዥዎችን መርምሮ የሚያጸድቅ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ያላቋቋመ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሚያዘጋጀው የግዥ እቅድ ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች ለይቶ ያላስቀመጠ መሆኑ፣
- ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያስፈልጉ የፈርኒቸር፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ ኮምፒውተር እና ተዛማጅ እቃዎች በታቀደላቸው ጊዜ ተገዝተው ያልቀረቡ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ቢዘረጋም ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የተገዙ ጀነሬተሮችና የምግብ ቤት እቃዎች በወቅቱ አገልግሎት ላይ አለመዋላቸው፣

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በየደረጃው ለግንባታ የሚያስፈልጉ የአርማታ ብረት ግብዓቶችን ብዛት በመለየት ግዥ ባለመፈፀሙ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ያላዋለ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር የስራ ተግባራትን ለሚያከናውኑ ባለሙያዎች ለስራቸው በሚያስፈልጉ የፌደራል መንግስት አዋጆች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች ላይ ስልጠና አለመስጠቱ፣
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታ ግብዓቶች ወጥነት ባለው መልኩ የሚመዘገቡበት አሰራር አለመኖሩ እና ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ያልተደረገላቸው መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ11ዱ ዩኒቨርሲቲዎች በሚገኙ የግንባታ ሳይቶች ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ እና ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ለሚያደርገው ክትትል ግብረ-መልስ ያልተሰጠ መሆኑ፣
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት (ሲሚንቶ እና የአርማታ ብረት) ቆጠራ ተካሂዶበት የሚያውቅ አለመሆኑ፣
- የንብረት አስተዳዳር ሰራተኞች መ/ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት የሚደረጉበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አገልግሎት የማይሰጥ ንብረት የሚወገድበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት እና አቅራቢዎች ጋር በቅንጅት በመስራት እና መደበኛ የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት በግዥና ንብረት አስተዳደር ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን በወቅቱ ያልፈታ መሆኑ

ታውቋል፡፡

98. ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ሊያሻሽሉ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች (Recommendations)

99. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የ11አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሆነ በሌሎች ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች እቅድ ሲያቅድ የሚያዘጋጃቸውን መመሪያዎች እና ሰነዶች ለይቶ ሊያስቀምጥ፣ የግዥ ዕቅድ ሲታቀድ ግብዓቱን ከሚጠቀሙ አካላት የግዥ ፍላጎት ሊያሰባስብ እና የገበያ ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡ የሚገዛቸውን ዕቃዎች በአይነትና ብዛት በመለየት አስቀድሞ ሊያስቀምጥ፣ ግዥዎቹ የሚከናወኑበትን ዘዴ በግልጽ በማስቀመጥ እንዲሁም ተግባራት የሚከናወኑበትን ጊዜ ሊያመላክት ይገባል፡፡ የግዥ ዕቅዱ የሚገዙ ዕቃዎች ብዛትና አይነት ከዚህ በፊት ተገዝተው በመጋዘን/ በግንባታ ቦታ ላይ ያሉትን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም በዕቅዱ መሰረት ስለመከናወኑ ከዕቅዱ ጋር በማነጻጸር በየጊዜው የእቅድ ክንውን ሪፖርት የሚቀርብበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚገዛቸው እቃዎች እንዲዘጋጁ ያደረጋቸውን የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫዎችና የግዥ ስምምነት ውሎች እቃዎቹን ለሚጠቀሙት ዩኒቨርሲቲዎች አስቀድሞ በመላክ በዝርዝር እንዲያውቁ እና እቃዎቹ በውሉ መሰረት ስለመቅረባቸው ለማረጋገጥም ሆነ ለእቃዎቹ ተገቢ ቦታ አስቀድሞ እንዲያዘጋጁ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ለትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ግዥ የቴክኒክ መግለጫዎች ዝግጅት ለማድረግ እና በተዘጋጁት መግለጫዎቹ መሰረት ዕቃዎቹ ስለመቅረባቸው የሚያረጋግጥ አማካሪ ቅጥርም በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በተዘጋጀው የእቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም ማንዋል መሰረት በግልጽ ጨረታ ሊከናወን እና ፈቃድ ባላቸው አካላት ሊሰራ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች ከፍተኛ ግዥዎችን መርምሮ የሚያፀድቅ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊያቋቁምና ግዥዎች የመንግስት ህግና ስርዓት ጠብቀው መግዛታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላት በማስተባበር ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስፈልጉ የመጽሐፍት፣ የፈርኒቸር፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ግብዓቶች ግዥ በወቅቱ በመፈፀም ለዩኒቨርሲቲዎቹ ሊያስረክብ እና አገልግሎት ላይ መዋላቸውን በመከታተል በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠውን ግብ ሊያሳካ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በራሱ ባለሙያዎች እና በቀጠራቸው አማካሪዎች አማካኝነት በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተገዙ የምግብ ማዘጋጃ፣ ማብሰያ እና ማቅረቢያ እቃዎችና ጄነሬተሮችን ለተጠቃሚ ዩኒቨርሲቲዎች በወቅቱ ሊያስረክብ እና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግዥ የተመደበለትን በጀት በሚሰራው ስራ ልክ በመለየት የመንግስት የግዥ ስርዓትን ጠብቆ በወቅቱና በአግባቡ ስራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር የስራ ተግባራትን የሚያከናውኑ ሰራተኞች የፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁ.649/2001፣ የአፈፃፀም መመሪያውን፣ የግዥ ማንዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና ሌሎች ተገቢ ቅፆች ይዘት እና አጠቃቀም እንዲያውቁ ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና ሊሰጣቸው እና የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን ለመፈፀም በቂ ክህሎት እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታ ግብዓች ግዥ፣ ስርጭት እና አጠቃቀም ወጥነት ባለው መልኩ ሊመዘገብ፣ የግዥ እና የጨረታ ሰነዶች በተገቢው መልኩ ሊጠበቁና ሊያዙ፣ እንዲሁም በየግንባታ ሳይቱ የሚገኙ የሲሚንቶ እና የአርማታ ብረቶች ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች በሚገኙ የግንባታ ሳይቶች ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ፣ ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ እና ግብዓቶች በትክክል መመዝገባቸውን መደበኛ ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ ሊሰጥ እና ችግሮች በወቅቱ እንዲቀረፉ ሊሰራ ይገባል፡፡

- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የንብረት ቆጠራ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የንብረት አስተዳዳር ሰራተኞች መ/ቤቱን/ ፕሮጄክቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት የሚደረጉበትንና እርክክብ የሚከናወንበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፕሮጀክቱ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች የሚመዘገቡበት፣ የሚከማቹበትና የሚወገዱበት የንብረት አወጋገድ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ቢደረግ ንብረቶቹን ከስርቆትና ከብክነት ለመከላከል እንዲሁም ከተቋራጮች የሚቀርቡ ተደጋጋሚ ጥያዎችን ምላሽ ለመስጠት ያግዛል፡፡
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት እና ከአቅራቢዎች ጋር በቅንጅት በመስራትና በግዥ ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት ችግሮቹን በወቅቱ ሊቀርፍና በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የተቀመጠውን ዕቅድ እንዲሳካ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ በኦዲት ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የወራቤ ዩኒቨርሲቲ፣ የእንጂባራ ዩኒቨርሲቲ እና የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ኃላፊዎች፣ እንዲሁም የግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት የስራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች(Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እስትራቴጂክ ዕቅድንና የግዥ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የግዥ ዕቅድ መርሃ ግብር በማዘጋጀት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም፣<br><br>1.1 የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ለሚፈጽማቸው ግዥዎች የግዥ ፍላጎት እና የግዥ መርሀ ግብርን መሰረት በማድረግ የግዥ እቅድ የሚያዘጋጅና በዕቅዱ መሰረት መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር የተዘረጋ መሆኑን መገምገም፣ | 1. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ ለሚሰራቸው ስራዎች ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር ስራዎችን በተመለከተ የሚሰራቸውን ስራዎች የእስትራቴጅክ እቅዱን ወደ ዓመታዊ እቅድ በመመንዘር ሊያቅድ እና የክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 3. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችሉ ግዥዎችን ለመፈፀም በእቃዎች ዓይነት፣ ብዛት እና ጥራት የግዥ ፍላጎቶችን ሊያሰባስብ ይገባል፡፡ |
| | 4. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በግዥ ሂደት ዋና ዋና ተግባራት የሚከናወኑበትን ጊዜ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ |
| | 5.ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በግዥ እቅድ ዝግጅት ወቅት ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች ውስጥ አግባብነት ያለውን በመምረጥ በእቅዱ ላይ ሊያመላክት ይገባል፡፡ |
| | 6. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የጽ/ቤቱን ከፍተኛ ግዥዎች መርምሮ የሚያፀድቅ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይገባል፡፡ |
| | 7. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ያዘጋጀውን ዓመታዊ የግዥ እቅድ በመ/ቤቱ ለተቋቋመው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አቅርቦ አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቅርቦ ሊያስፀድቅ ይገባል፡፡ |
| | 8. ግዥ ፈፃሚ አካላት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት በማንኛውም ጊዜ የግዥ ዕቅዳቸውን ሲያሻሽሉ የተሻሻለው የግዥ እቅድ እንዲጸድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 9. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ግዥ አፈፃፀም ሂደት በፀደቀው የግዥ እቅድ መሰረት መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች(Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | 10. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የፀደቀ የግዥ እቅድ መሰረት በማድረግ የሚገዙ እቃዎች ወይም አገልግሎቶችን የያዘ ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ሊያዘጋጅ ወይም እንዲዘጋጅ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 1.2 የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የግዥ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣ | 11. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች የገበያ ጥናት ሊያከናውን ይገባል፡፡ |
| | 12. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በግልፅ ጨረታ ሊያከናውን ይገባል፡፡ |
| | 13. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች በሚጠቀምበት ጊዜ በነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 14. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚያወጣው የጨረታ ጥሪ በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ አገራዊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ጊዜ ታትሞ ሊወጣ ይገባል፡፡ |
| | 15. የትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ግዥ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ኃላፊነት ለዚሁ ስራ በጨረታ በሚቀጠር አማካሪ ድርጅት ሊከናወን ይገባል፡፡ |
| | 16. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያስፈልጉ የፈርኒቸር፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን፣ የትምህርት መሳሪያዎችን፣ ኮምፒውተር እና ተዛማጅ እቃዎችን በታቀደላቸው ጊዜ ግዥ ሊፈፅም ይገባል፡፡ |
| | 17. አቅራቢ ድርጅቶች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር በገቡት ውል መሰረት እቃውን ካላቀረቡ ወይም አገልግሎት ካልሰጡ ጽ/ቤቱ በውሉ መሰረት አቅራቢው ያስያዘውን የውል ማስከበሪያ ሊወርስ ይገባል፡፡ |
| | 18. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለግዥ የተመደበለትን በጀት የመንግስት የግዥ ስርዓትን ጠብቆ በወቅቱና በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል ይገባዋል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች(Evaluative Criteria) |
| --- | --- |
| | 19. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር የስራ ተግባራትን የሚያከናውኑ ሰራተኞች የፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁ.649/2001፣ የአፈፃፀም መመሪያውን፣ የግዥ ማንዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና ሌሎች ተገቢ ቅፆች ይዘት እና አጠቃቀም እንዲያውቁ ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና ሊሰጣቸው እና የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን ለመፈፀም በቂ ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | 20. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አቅራቢዎች እቃዎችን ሲያስረክቡ በትክክል በቴክኒክ መግለጫ /specification/ እና በቀረበው ናሙና መሰረት መሆኑን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 21. ፕሮጀክት ጽቤቱ የተገዙ ዕቃዎችን የግዥ ጥያቄ ላቀረበው ክፍል ወይም ቅርንጫፍ በወቅቱ ሊያሰራጭ እና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 22. በግዥ ውል በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እቃዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላዘገዩበት ጊዜ በቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ ሊያስከፍል እና አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | 23. በግዥ ሂደት ላይ በሚሰጥ ውሳኔ የቅሬታ አቀራረብና ምላሽ አሰጣጥ ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| 2. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የንብረት አስተዳደር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ | 24. የ11ዱ ዩኒቨርስቲዎች ፕሮጀክት ጽ/ቤት ንብረት በሚገባ የተመዘገበ እና ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግለት ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 25. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት በጥንቃቄ ስለመያዙ እና ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ጽ/ቤቱ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 26. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ ሊካሄድበት ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች(Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | 27. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የንብረት ቁጥጥር ስርዓት መሰረታዊ የንብረት መዛግብቶችን (ስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ) መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 28. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የንብረት አስተዳዳር ሰራተኞች መ/ቤቱን በሚለቁበት ጊዜ የንብረት ገቢ ወጪ ኦዲት ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 29. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ንብረት አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ የሚወገድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 30. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሂደት ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን በየጊዜው በመቅረፍ የተሻለ አሰራር ሊፈጥር ይገባል፡፡ |
| 3. የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የግዥና ንብረት አስተዳደር በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤ | 31. በ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች በሚገኙ የሳይት ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች እና በትምህርት ሚኒስቴር በሚገኘው ፕሮጀክት ጽ/ቤት መካከል መደበኛ የሪፖርት ልውውጥ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 32. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ዓላማውን ለማሳካት ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት እና ከአቅራቢዎች ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 33. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከአቅራቢዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በግዥ ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መደበኛ የመወያያ መድረኮችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 34. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግዥ ሠነዶችንና መረጃዎችን በዘመናዊ ቴክኖሎጅ በማስደገፍ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 35. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከሚመለከታቸዉ የመንግስት መ/ቤቶች እና ከአቅራቢዎች ጋር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ፣ ስርዓት ሊፈጥር ይገባል፡፡ |

# አባሪ 2፡ የ11ዱ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ድርጅታዊ መዋቅር

